ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ረቡዕ
83ኛ ዓመት ቁጥር 121 ጥር 1 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

# "የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲን ለሀገራችን ልማት ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ አድርገን እየሠራን እንገኛለን"

- አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ


ፎቶ፡ ከፋ ደስ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲን ለሀገራችን ልማት ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ አድርገን እየሠራን እንገኛለን ሲሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ ገለጹ፡፡ የፖለቲካ ዲፕሎማሲው የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲውን ማዕከል እንዲያደርግ እየተሠራ መሆኑንም አመላክተዋል፡፡

አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ሠላምና የሀገር ውስጥ ልማትን በሚያረጋግጡ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡

በዲፕሎማሲው ዘርፍ ዋነኛ የትኩረት ማጠንጠኛ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል የኢኮኖሚው ዲፕሎማሲ አንዱ መሆኑን አስረድተዋል።

በዲፕሎማሲው መስክ አዳዲስ የሥራ ስምምነቶች ተደርገዋል ያሉት አምባሳደር ምስጋኑ፤ በተጨማሪም በዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ መስክ በተለያዩ ሀገራት ያሉ ኢትዮጵያውያን መብታቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ ጥረት መደረጉን ተናግረዋል።

የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው ተጨማሪ የኢንቨስ ትመንት፣ የቴክኒክና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማምጣት አለበት ያሉት አምባሳደር ምስጋኑ፤ የሀገር ውስጥ የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች በውጭ ሀገራት የዲፕሎማሲ ግንኙነቶች እንዲታገዙ በማድረግ ልማትን ለማፋጠንና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማምጣት ሰፊ ጥረት ተደርጓል ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ምርቶችን የገበያ ተደራሽነት ለማሳደግ፣ ቱሪዝሙን በማስተዋወቅ፣ የውጭ ኢንቨስትመንት ከመሳብ አኳያ የቢዝነስና የኢንቨስትመንት ፎረሞችን በማዘጋጀት እንዲሁም አዳዲስ የገበያ ትስስሮችን በመፍጠር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በትኩረት እየተሠራ እንደሆነ አምባሳደር ምስጋኑ አመላክተዋል፡፡

"የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲን ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# በከተማ አስተዳደሩ ለሠራተኞችና አመራሮች በተሰጠው ፈተና፡-

- 50 ከመቶ ፈጻሚዎች እና 34 በመቶ አመራሮች የማለፊያ ነጥብ አምጥተዋል
- ማለፊያ ውጤት ሳሳመጡት ሥልጠና ተሰጥቶ ወደሌላ የሥራ መደብ ይመደባሉ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- ለ15 ሺህ 151 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሠራተኞችና አመራሮች በተሰጠው ፈተና 6 ሺህ 517ቱ የማለፊያ ነጥብ ማምጣታቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ።

ለፈተና ከተቀመጡ 10 ሺህ 257 ፈፃሚዎች 5 ሺህ 95 ወይንም ከ50 በመቶ በላይ የሚሆኑት የማለፊያ ውጤት ማስመዝገብ የቻሉ ሲሆን ፈተናውን ከወሰዱት 4 ሺህ 213 አመራሮች ማለፊያ ውጤት ያስመዘገቡት 34 በመቶ ወይንም 1 ሺህ 422 መሆናቸውንም ገልጿል፡፡

ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሠራተኞች ሲሰጥ የነበረውን ፈተና በሚመለከት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ

በከተማ አስተዳደሩ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia






# "ኢትዮጵያ ከሱማሊላንድ ጋር ያደረገችው የባሕር በር ስምምነት የሚገባትን ከፍታ ለመያዝ ያስችላታል"

- አምባሳደር ጥሩነህ ዜና
የቀድሞ ዲፕሎማትና የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከሰሞኑን ከሱማሊላንድ ጋር ያደረገችው የባሕር በር ስምምነት የሚገባትን ከፍታ ለመያዝ የሚያስችላት ነው ሲሉ የቀድሞ ዲፕሎማትና የሰብዓዊ መብት

"ኢትዮጵያ ከሱማሊላንድ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## ማኅበራት በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚኖራቸውን ሚና ለማሳደግ ሪፎርም እየተሠራ ነው

ገጽ 8








ኢንጂነር ሱልጣን ዋሊ (ዶ/ር)

# የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ

## ከአካባቢ ጥበቃ ባሻገር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እያስገኘ ነው

- ከ180ሺ በላይ ሰዎች የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ሆነዋል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ካርበንዳይ አክሳይድ ወደከባቢው እንዳይለቀቅ በማድረግ የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ላይ አወንታዊ ሚና ከመጫወቱም ባሻገር ዘርፈብዙ ጠቀሜታ እያስገኘ መሆኑን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ገለጸ። በኢትዮጵያ ከ180 ሺ በላይ ሰዎች የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ መሆናቸውም ተጠቁሟል።

“በኢትዮጵያ አየር ንብረት ለውጥ የመቋቋም አቅምን ማጎልበት፣ ንጹሕ ማብሰያ እና ምርታማነትን ማሳደግ” በሚል መሪ ሀሳብ የባዮ ጋዝን አጠቃቀም ማሳደግን በተመለከተ ሲካሄድ የነበረው ውይይት የመዝጊያ መርሐ ግብር ትናንት ተካሂዷል።

በመርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዴኤታው ኢንጂነር ሱልጣን ዋሊ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች አሉት። ቴክኖሎጂው ለማብሰያነትና ብርሃን ለመስጠት ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ ኮምፖስት እና የተፈጥሮ ማዳበሪያ ለመሥራት ከፍተኛ ጠቀሜታ እየሰጠ ነው። ይህም ምርትና ምርታማነታችንን ያሳድጋል።

የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂን በመጠቀምም ሁለት ሚሊዮን ቶን ካርበንዳይኦክሳይድ ወደ የአካባቢው እንዳይለቀቅ መደረጉን ጠቁመው፤ ቴክኖሎጂው ከ140 ሺ ሄክታር በላይ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በማምረት የግብርና ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ አቅም እንዳለውም ገልጸዋል። በአሁኑ ጊዜም ከ180ሺ በላይ ሰዎች የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ምግብ ለማብሰል አብዛኛው ማኅበረሰብ ማገዶ ተጠቃሚ በመሆኑ ደንን መጨፍጨፍ፣ የመሬት መሸርሸር፣ ምርትና ምርታማነት የመቀነስ እንዲሁም የምግብ ዋስትና እንዳይረጋገጥ ያደርጋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ከዚህ አኳያም የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

እናቶችና ሕጻናት በማገዶ እንጨት ጭስ ለበሽታ እንዳይዳረጉ የሚያደርግ በመሆኑም በሽታን ለመከላከል እንደሚያግዝ አክለው ገልጸዋል።

በባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ፕሮግራም አንድ ሺህ 700 አባወራዎችን በግንባታ ሥራ በማሰማራት የሥራ ዕድል እንደተፈጠረላቸው የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ባለው የባዮ ጋዝ ፕሮግራም ግምገማ ቴክኖሎጂው ከ 86 በመቶ በላይ ስኬታማ መሆኑን ተናግረዋል።

ፕሮግራሙ በአውሮፓ ኅብረት ሲደገፍ መቆየቱን አመላክተው፤ ኅብረቱ 21 ሚሊየን ዩሮ ድጋፍ አድርጓል ብለዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥትም ለፕሮግራሙ የፋይናንስ ድጋፍ ማድረጉን ገልጸው፤ በቀጣይ የተጠቃሚውን ቁጥር ለማሳደግ እንደሚሠራም ጠቁመዋል።

በመርሐ ግብሩ ላይ የአውሮፓ ኅብረት ተወካዮች፣ የባዮ ጋዝ ተጠቃሚዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተገኙ ሲሆን ለአውሮፓ ኅብረትም እውቅና ተሰጥቷል።

# በመዲናዋ በአምስት ወራት

## በከተማ ግብርና ስድስት ሺህ ለሚጠጉ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ባለፉት አምስት ወራት ውስጥ በከተማ ግብርና ስድስት ሺህ ለሚጠጉ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር ፋሩቅ ጀማል ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት በአዲስ አበባ በከተማ ግብርና ዘርፍ ለ23ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል። ባለፉት አምስት ወራት ውስጥ ለአምስት ሺህ 981 ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

የሥራ ዕድሉ የተፈጠረው በእንስሳት እርባታ፣ በጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት እንዲሁም በተለያዩ የግብርና ሥራዎች መሆኑን አስረድተዋል።

በመዲናዋ ለከተማ ግብርና የሚሆን ሰፊ የሰው ኃይልና የተፈጥሮ ሃብት መኖሩን አመላክተው፤ ዜጎች ባላቸው አነስተኛ ቦታ ላይ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን በማዘጋጀት እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን መደጎም እንደሚገባቸው ጠቁመዋል።

በቀጣይ ዘርፉን ለማነቃቃት የንቅናቄ ሥራ እንደሚከናወን አስታውቀው፤ በሦስት ወራት ውስጥ በከተማ ግብርው ዘርፍ በማኅበር ለሚደራጁ ለ10 ሺህ ወጣትና ሴቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በዶሮ እርባታ፣ በወተት ላም፣ በከብት ማደለብ፣ በአትክልት ልማት፣ በችግኝ ማፍላትና በሌሎች የሥራ መስኮች ዜጎች በምርጫቸው ወደቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች በመግባት የክህሎት መር ሥልጠና እንዲወስዱና ወደሥራ እንዲሠማሩ ይደረጋል ሲሉ ጠቁመዋል።

ለዜጎች የመሥሪያ ቦታ፣ የገበያ ትስስርና በባንክ አማካኝነት የገንዘብ ብድር አገልግሎት እንደሚመቻች አስታውቀው፤ በአዲስ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አክስዮን ማኅበር በኩል ደግሞ የተለያዩ ማሽኖችን በሊዝ ብድር እንዲያገኙ እንደሚደረግ ምክትል ኮሚሽነሩ አስታውቀዋል።

የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽንም ወደሥራ ለሚሰማሩ ዜጎች የተለያዩ ሙያዊ ድጋፎችን ያደርጋል ሲሉ ጠቁመው፤ ለሥልጠናው ልየታ በማድረግ ሥራ አጥ ዜጎች እንደሚመለመሉ ተናግረዋል።



የሥራ ዕድሉ ተጠቃሚ መሆን የሚፈልግ ማንኛውም ዜጋ ተደራጅቶ በመምጣት ዕድሉን ሊጠቀም እንደሚገባ አንስተዋል፡፡

ወጣቶች ሥራን ሳይንቁ በከተመኛ ግብርና በመሳተፍ ድህነትን ማሸነፍ ይገባቸዋል ያሉት አቶ ፋሩቅ፤ የከተማ ግብርና አዋጭ በመሆኑ በተለይም ወጣቶች በዘርፉ በመሠማራትና ጠንክሮ በመሥራት በፍጥነት ወደኢንቨስትመንት የሚሸጋገሩበት ዕድሉ እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡

# ቀጣዩ የአየር ሁኔታ ለድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ ቀናት የሚኖረው የአየር ሁኔታ በአሁኑ ወቅት በመከናወን ላይ ለሚገኘው የድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል ሲል የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

ኢንስቲትዩቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መረጃ እንዳመለከተው፤ በቀጣይ ቀናት የሚኖረው የአየር ሁኔታ በአሁኑ ወቅት በመከናወን ላይ ለሚገኘው የድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

በመረጃው መሠረት፤ በደቡብ አጋማሽና በመካ ከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው እርጥበት ዘግይተው ለተዘሩ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑትና ጥምር ግብርና ለሚያካሂዱት ለደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ለሚያከናውኑት የእንስሳት ልማት ጥሩ ነው፡፡ ለሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርም ይጠበቃል፡፡

በሰሜን ምሥራቅ፣ በመካከለኛው እና በምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሣርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር ጠቀሜታ እንደሚኖረውና የበልግ ወቅትን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት እንዲችሉ ጠቀሜታ እንደሚኖረውም አስታውቋል፡፡

በመጀመሪያው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፤ ፀሐያማውና ነፋሻማው አየር ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረው አኃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡባዊና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ይኖራቸዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አኃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምሥራቅ፤ በመካከለኛውና በምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል በምሥራቅ አማራ፤ መካከለኛውና በምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሸየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ የጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂና የቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የመካከለኛው ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡

በተጨማሪም ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፤ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች እንዲሁም የሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ የሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ባሌ፣ ምሥራቅ ባሌ፣ የምሥራቅና የምዕራብ ሐረርጌ እንዲሁም ድሬዳዋና ሐረሪ፤ የመካከለኛው፣ የምሥራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች እንዲሁም ከአፋር ክልል ዞን 2፣ 4፣ 3 እና 5 ቀላል መጠን ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ያገኛሉ።

በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናትም በምሥራቅ አማራ፤ በመካከለኛው እና በምሥራቅ የሀገራችን አካባቢዎች ላይ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚስተዋል አኃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ ሲል መረጃው ጠቁሟል ፡፡

ዜና

# ዩኒቨርሲቲው የቆዳ በሽታን ለማከም የሚውሉ መድኃኒቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ሙከራ ላይ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ባሕላዊ ሕክምናዎችን በሳይንስ በመደገፍ የቆዳ በሽታን ለማከም የሚውሉ መድኃኒቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ሙከራ ላይ መሆኑን የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ።

የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ንጉሥ ታደሰ(ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው ለቆዳ በሽታ የሚሆኑ መድኃኒቶችን ቀምሞ ለማውጣት እየሠራ ነው።

ባሕላዊ የሕክምና እውቀቶችን በሳይንስ ደግፎ ማሳደግና እውቀቱ እንዳይሞት ሽግግር ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ንጉሥ፤ ከዚህ አንጻር የሀገር በቀል እውቀትን ለማስተማርና ለማበልጸግ የሚረዳ በአንኮበር የዕፅዋት ማዕከል እየተቋቋመ ነው ብለዋል።

ቆዳን የሚያሳክኩ በሽታዎችን ለማከም የሚውሉ ሦስት ምርቶች በሙከራ ላይ ናቸው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ እነዚህም በቅባት መልክ የሚቀርቡ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ዶክተር ንጉሥ እንደተናገሩት፤ ምርቶችን በዚህ ዓመት ይፋ የማድረግ ሀሳብ አለ። ነገር ግን የፀጥታው ሁኔታ ተዘዋውረው እንዳይሠሩ አድርጓቸዋል። ሆኖም ወደፊት ለገበያ በማቅረብ ኅብረተሰቡ ተጠቃሚ እንደሚሆን ይጠበቃል።

መድኃኒት መቀመምና ወደ ምርት መቀየር ረጅም ጉዞን ይፈልጋል ያሉት ዶክተር ንጉሥ፤ መድኃኒቶችን እውን ለማድረግ ብዙ ርቀት ተጉዘናል። በተለይ አስፈላጊ



አዝመራው አየሁ (ዶ/ር)



ንጉሥ ታደሰ (ዶ/ር)

የላብራቶሪ እቃዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ መሥራት ፈታኝ ቢሆንም መምሕራን እየለፉ ነው። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በእንስሳት ላይ ተሞክሮ ውጤቱ ጥሩ መሆኑ ተረጋግጧል። ተግባራዊ ለማድረግ በቀጣይ በምርምር ሥነምግባር መሠረት በሰዎች ላይ ተሞክሮ መረጋገጥ አለበት። ጥንቃቄ የሚፈልግ በመሆኑ እንደ ሀገር የተቀመጡ መስፈርቶችን ማለፍ ይኖርበታል ብለዋል።

በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዚዳንት አዝመራው አየሁ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ዩኒቨርሲቲው በትኩረት ከሚሠራባቸው ዘርፎች ውስጥ ጤና አንዱ መሆኑን ጠቁመው፤ በባሕላዊ የሕክምና ዘርፍ የሀገር በቀል እውቀት አቃቢዎች (አዋቂዎች)ን እውቀት በሳይንስ በመደገፍና በማበልጸግ ወደ ማኅበረሰቡ የምንመልስበትን ሥርዓት እየፈጠርን ነው ብለዋል።

ሰሜን ሸዋ አካባቢ ለዘመናት በሰውና በእንስሳት ላይ ጥቅም ላይ በሚውሉ እፅዋቶች የበለጸገ መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር አዝመራው፤ የሀገር በቀል አቃቢዎችም በብዛት የሚገኙበት አካባቢ በመሆኑ እውቀታቸውን ተጠቅሞ በሳይንስ በመደገፍ ወደ ጤና ሕክምና ሥርዓት ውስጥ የምናጋምድበትን መንገድ እየፈለግን ነው ብለዋል።

“ረጅም ጊዜ ቢወስድም ለቆዳ ሕክምና የሚውሉ የተወሰኑ ምርቶችን ለማውጣት በቅድመ በዝግጅት ላይ ነን። በሙከራ ደረጃ ያሉት መድኃኒቶች ለቆዳና ለተያያዙ በሽታዎች ሕክምና የሚውሉ ናቸው” ሲሉም ተናግረዋል።

ሀገር በቀል እውቀትን በዘመናዊ መልክ ወደ መድኃኒትነት የመቀየር ሥርዓቱ እንደ ሀገር ባለመኖሩ ዩኒቨርሲቲው ፋና ወጊ ነው ያሉት ዶክተር አዝመራው፤ የመጀመሪያውን የክሊኒካል ሙከራ እየተካሄደ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በእንስሳት ላይ የሚደረገውን የሙከራ ሂደት መጨረሻውንና ዩኒቨርሲቲው የራሱን ምርት ራሱ ሞክሮ ወደ ገበያ ለማውጣት ሕጉ ስለማይፈቅድ የአርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት ሙከራውን እያካሄደ እንደሆነም ጠቁመዋል።

“የሥነምግባር ሂደቶችን በማለፍና ጉዳት ቢደርስ በሚል በሳይንሱ መሠረት የመድን ዋስትና በመግባት በሰዎች ላይ እየተሞከረ ነው። የመጀመሪያውን ደረጃ አልፏል፤ ሁለተኛው ደረጃ ሲጠናቀቅ ወደ ምርት በመቀየር ከማኅበረሰቡ የወጣውን እውቀት ሳይንስ ተጨምሮበት ወደ ገበያ ይቀርባል” ሲሉም ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር አዝመራው ገለጻ፤ መድኃኒቶች ወደ ገበያ ሲቀርቡ ለሰዎች ተስማሚ መሆን አለባቸው። በሙከራ ሂደቱ የሀገር በቀል አቃቤዎች ሚና ትልቅ ነበር። የሀገር በቀል እውቀትን በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የማካተት ሙከራዎችም አሉ። ቻይናና ሕንድ በሀገር በቀል እውቀት ትልቅ ተሞክሮ ያላቸው በመሆኑ ከነሱም በቅርበት እየተሠራ ነው።

# በክልሉ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓትን በመጠቀም የዜጎችን ኑሮ ለማሻሻል እየተሠራ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል እየተሠራ መሆኑ ተገለጸ፡፡

በክልሉ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ዙሪያ ትናንትና የምክክር መድረክ ሲካሄድ የተገኙት በኦሮሚያ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ክላስተር አስተባባሪ አቶ አብዱራህማን አብደላ እንደገለጹት፤ በክልሉ በተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና የተሻለች ሀገር ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ዘመናዊ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓትን ሥራ ላይ ማዋል የአሁኑ ትውልድ ኃላፊነት ነው ያሉት አቶ አብዱረህማን፤ በመሬት ሀብት ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ይበልጥ መሥራት ይገባል ብለዋል።

ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማምጣት የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት ወሳኝ መሆኑን ጠቅሰው፤ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓትን ማዘመን የተሻለችና ለኑሮ ምቹ የሆነች ሀገርን ለመጪው ትውልድ ለማውረስ የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል።

በክልሉ የመሬት አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን ለማዘመን እየተሠራ መሆኑን የጠቆሙት አቶ አብዱራህማን፤ መንግሥት በአረንጓዴ አሻራ መርሐግብርና በተፋሰስ ልማት የተጎዱ የመሬት ሀብቶች አገግመው ለልማት እንዲውሉ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

መሬትና የተፈጥሮ ሀብቶች የነገውን ትውልድ ዕድል የሚወስኑ በመሆናቸው የመሬት ሀብትን በእቅድና በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል ብለዋል።

የኦሮሚያ መሬት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጉታ ላቼሬ በበኩላቸው፤ በክልሉ በተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል እየተሠራ ነው፡፡

መሬትን ለላቀ አገልግሎት ለማዋል አጠቃቀምንና አስተዳደሩን ማዘመን አስፈላጊ ነው ያሉት አቶ ጉቱ፤ በክልሉ የመሬት አስተዳደር ሥርዓቱን ዲጂታላይዝ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።



አቶ አብዱራህማን አብደላ



አቶ ጉታ ላቼሬ

በካዳስተር ሥራው በከተማና በገጠር ስር የሚገኘው የመሬት ሀብት በሕገወጥ መንገድ እንዳይወረር እየተደረገ መሆኑን ገልጸው። የመሬት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን በቴክኖሎጂ በሚገኝ የማዘመን ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

መሬትን ለላቀ አገልግሎት ለመጠቀም ኅብረተሰቡን ያሳተፈና ዘመናዊ አሠራርን የተከተለ አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑን ጠቁመዋል።

በመርሐግብሩ ላይ ከፍተኛ የፌዴራልና የክልል ሥራ ኃላፊዎች፣ የተለያዩ ፕሬዚዳንቶችና ምሑራን እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

# ስምምነቱ የወጣቱን የወደፊት ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ዕድል ይፈጥራል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከሶማሌ ላንድ ጋር የተፈራረመችው የባሕር በር ስምምነት ብሔራዊ ጥቅምን በማስጠበቅና የወጣቱን የወደፊት ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ዕድል እንደሚፈጥር የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌደሬሽን ገለጸ። የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር የተፈራረመችውን የመግባቢያ ሰነድ ተከትሎ ትናንትና መግለጫ ሰጥቷል።

በወቅቱ የፌዴሬሽኑ የጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሙህዲን ናስር እንዳመለከቱት፤ ስምምነቱ የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅና የወጣቱን የወደፊት ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ዕድል የሚፈጥር ነው።

የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቀውሶችን በመቀልበስ ከጎረቤቶቻችን ጋር በጋራ የማደግ መርሕን መሠረት ያደረገ ስምምነት ነው ያሉት አቶ ሙህዲን፤ የትውልዱ ድል የሆነውን ስምምነት ተፈጻሚ ለማድረግ ወጣቱ ቁርጠኛ መሆን እንዳለበት ተናግረዋል።

ወጣቱ በታሪክ አጋጣሚ የተገኘውን የባሕር በር ስምምነት እውን እንዲሆን በጋራ መሥራት አለበት ያሉት አቶ ሙህዲን፤ ስምምነቱ ኢትዮጵያ በቀጣናው እንዲሁም በዓለም አደባባይ ተገቢው ስፍራ እንድታገኝ የሚያግዝ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ሙህዲን አክለውም ስምምነቱ በኢትዮጵያ ወጣቶች ዘንድ ላለፉት ሦስት አስርተ ዓመታት የዘለቀው የወደብ አልባነት ስሜት የሚቀይር እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

የሀገሪቱ የረዥም ጊዜ የኢኮኖሚ ጥያቄ የሆነውን የወደብ ጉዳይ ሁሉን አካታች በሆነና የጋራ ተጠቃሚነትን ባረጋገጠ መልኩ የሚሳካበት መንገድ መመቻቸቱ ለአፍሪካ ቀንድ ልማትና ብልጽግና ትልቅ እምርታ ያመጣል ሲሉ አስረድተዋል።

ስምምነቱ የኢትዮጵያውያንን የዘመናት ጭንቀትና ቁዘማ ለማከም የሚያስችል አጋጣሚ ከመፍጠሩም በላይ በጋራ ተባብሮ ለማደግ ያለው ራዕይና ጉጉት በተግባር የታየበት መሆኑን አቶ ሙህዲን አመላክተዋል፡፡

የመግባቢያ ሰነዱ ሁለቱንም ተጠቃሚ በሚያደርግ አግባብ ተፈርሟል ያሉት የጽሕፈት ቤት ኃላፊው፤ ኢትዮጵያ በኤደን ባሕረሰላጤ ላይ ዘላቂና አስተማማኝ የባሕር ኃይል ቤዝና የንግድ ማሪታይም አገልግሎት በሊዝ የምታገኝበትን ዕድል የሚያስገኝ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡



አቶ ሙህዲን ናስር

እንደ አቶ ሙህዲን ገለጻ፤ በቀጣናው ሰፊ ፀጋዎች በመኖራቸው በክፋት ተሸብቦ ትብብርን መንፈግ በሕዝቦች ጉስቁልና የሚሰነዘር ዝቅታን ከማባባስ በዘለለ የተሻለ ነገን ለመፍጠር አይቻልም።

የተደረገው ስምምነት መንግሥት የኢትዮጵያን መሻቶች ከጎረቤቶቿ ጋር በሚደረግ ትብብር፣ በሰጥቶ መቀበልና በሠላማዊ መንገድ ብቻ ለማሳካት ያለውን እምነት በተግባር ያሳየበት እንደሆነም ነው አቶ ሙህዲን የተናገሩት፡፡

ስምምነቱ በዘመናት አንዴ የሚከሠት የታሪክ እጥፋት ነው ያሉት የጽሕፈት ቤት ኃላፊው፤ ልዩነቶችን ወደ ጎን በመተው ከመቼውም ጊዜ በላይ በማቻቻልና ተያይዞ በመቆም የተገኘውን መልካም አጋጣሚ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ወጣቱ በታሪክ ተወቃሽ እንዳይሆን የበኩሉን እንዲወጣና ባገኘው አጋጣሚ የሀገሩ መልካም ገጽታ እንዲገነባ አቶ ሙህዲን መልዕክት አስተላልፈዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዘመናትን የተሻገረው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ጉዞ !

ኢትዮጵያ ጥንታዊ የዲፕሎማሲ ታሪክ ካላቸው ሀገራት አንዷ ነች፡፡ ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በሃይማኖት በባሕልና በንግድ  እንቅስቃሴ ከበርካታ ሀገራት ጋር የጠነከረ ግንኙነት መሠረት የጣለችና በዲፕሎማሲው መስከም ተጠቃሽ ተሞክሮ ማዳበር ከመቻሏም ባሻገር ከንግሥት ሳባ እስከ ዘመነኛው የዲጂታል ዲፕሎማሲ ድረስ ዕምቅ ታሪክና ተሞክሮ ያላት ሀገር ነች፡፡

በየዘመናቱ የነበሩ የኢትዮጵያ መሪዎችም ሀገሪቱን ከውጭው ዓለም ጋር የሰመረ ግንኙነት እንዲኖራትና አልፎ ተርፎም ተፅዕኖ ፈጣሪ ሀገር እንድትሆን ዘርፈ ብዙ ግንኙነቶችን ሲመሠርቱ ቆይተዋል፡፡ በዘመነ አክሱም የዲፕሎማሲ ዘመን የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲያዊ መሠረቶች ተጥለዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል በንጉሥ ኢዛና ዘመን ንግድና ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ ግንኙነቶች ተፈጥረዋል፡፡

ወደ መካከለኛው ዘመን ስንመጣ የዲፕሎማሲው ዋነኛ አቅጣጫ የሀገርን ሉዓላዊነትና አንድነትን ማጽናት ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ከውስጥም ከውጭም የሚመጡባትን የሉዓላዊነት አደጋዎች በመጋፈጥና አንድነቷን አስጠብቆ መሄድ የዲፕሎማሲው ቁልፍ አቅጣጫ ነበር፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ በየዘመናቱ የሚያጋጥማትን የሉዓላዊነት ፈተናዎች በማለፍ ዛሬ ላይ ደርሳለች፡፡ በተለይም እንደሀገር ለዲፕሎማሲና ለውጭ ግንኙነት ትኩረት ከተሰጠ 116 ዓመታት የተቆጠሩ ሲሆን በእነዚህ ዓመታት በርካታ ፈተናዎችንና ስኬቶችን በማስመዝገብ ኢትዮጵያን ከነሙሉ ክብሯ ለዛሬው ትውልድ ለማስረከብ ተችሏል፡፡

116 ዓመታትን ያስቆጠረው የኢትዮጵያ ዘመናዊ ዲፕሎማሲ በተለይ ባለፉት አምስት ዓመታት አዳዲስ ገጽታዎችን በመላበስ አድማሱን አስፍቶ ቀጥሏል፡፡ በተለይም ለቀጣናዊ ግንኙነት የመጀመሪያውን ትኩረት በመስጠት ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የጠበቀ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዲኖራት ተደርጓል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ወደ ሥልጣን በመጡ በጥቂት ቀናት ውስጥ የመጀመሪያ የውጭ ጉዟቸውን ያደረጉት ወደ ጎረቤት ሀገር ጂቡቲ ነው፡፡ ጂቡቲ ለኢትዮጵያ 95 በመቶ የወደብ አገልግሎት የምትሰጥ በመሆኗ እና ሁለቱ ሀገራት በኢኮኖሚው መስክ ከፍተኛ ትስስር ያላቸው ከመሆናቸው አንጻር ከጎረቤት ሀገራት ጂቡቲን ማስቀደማቸው ተገቢ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ከዚያም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀኑት ወደ ሱዳን ሲሆን በቀውስ ውስጥ የነበረችውን ሀገር ወደ ተሻለ መረጋጋት የሚወስድ የአስታራቂነት ሚና  ተጫውታለች፡፡

ለ20 ዓመታት ያህል በጦርነት ስጋት ውስጥ የቆዩትን ኢትዮጵያንና ኤርትራን በማስታረቅና ግንኙነታቸውንም ወደ ተሻለ ደረጃ በማድረስ ቀጣናዊ ዲፕሎማሲው ወደ ከፍታ እንዲሸጋገር ኢትዮጵያ የመሪነቱን ሚና ተጫውታለች፡፡

ሌላው ባለፉት አምስት ዓመታት በዲፕሎማሲው መስክ ላይ የታየው እምርታ ኢትዮጵያ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ መከተሏ ነው፡፡ አዲስ በሆነው በዚህ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው በክብር ለመመለስ ችለዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) በሱዳን በነበሩበት ወቅት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በእስር ቤት ይኖሩ የነበሩትን በማስፈታት በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ለመጀመሪያ ጊዜ ራሳቸው በተሳፈሩበት አውሮፕላን ከልዑካቸው ጋር ወደ ሀገር ቤት እንዲጓዙ ማድረጋቸው መንግሥታቸው ለዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ያለውን ቁርጠኝነት ያሳየ ነበር፡፡

ለበርካታ ሀገራት በምሳሌነት የሚጠቀስና የዘመናዊ ዲፕሎማሲ አዲስ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ አንዱ ክስተት ኢትዮጵያ የተከተለችው አረንጓዴ ዲፕሎማሲ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት ከ32 ነጥብ 5 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል ለዓለም ውለታ ውላለች አስደንቃለች፡፡ በእነዚሁ ዓመታት አረንጓዴ አሻራ የአካባቢው መድኅን መሆኑን በመረዳት ከራሷ አልፎ የጎረቤት ሀገራትም ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞች ወደ ጎረቤት ሀገራት በመላክና አብሮ በመትከልም የጋራ አካባቢን በጋራ የመጠበቅ መርሕ እውን እንዲሆን መሠረት ጥላለች፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም የጎረቤት ሀገራት በኃይል አቅርቦት እንዲተሳሰሩ ኢትዮጵያ እያከናወነችው ያለችውም ተግባር አንዱ  የኃይል አቅርቦት ዲፕሎማሲ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከዓባይ ግድብ  እና ከግልገል ግቤ ሦስት የኃይል ማመንጫዎች የምታገኘውን ኃይል ከራሷ አልፋ የጎረቤት ሀገራትን ልማት እንዲያቀላጥፍ ለኬንያ፤ ለጅቡቲ፤ ለሱዳን፤ ለደቡብ ሱዳን ኃይል በማቅረብ ላይ ትገኛለች፡፡

ዘመናትን የዋጀው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ጉዞ ሀገርን አጽንቶ ሕዝብን ማዕከል አድርጎ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ ዛሬም ግስጋሴውን ቀጥሎ ከሀገር አልፎ ቀጣናዊ ትስስርን ማዕከል አድርጎ ዕይታውን አስፍቷል፡፡ ከመንግሥት ለመንግሥት ግንኙነት አልፎ ወደ ኢኮኖሚያዊና ቀጣናዊ ትስስር የሰፋው ዲፕሎማሲዊ ግንኙነትም አዲስ ገጽታ የተላበሰ ከመሆኑም ባሻገር ኢትዮጵያን በዲፕሎማሲው መስክ ያላትን ተፅዕኖ ፈጣሪነት የሚያጎላ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## እውቅና ሊሰጠው የሚገባው የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት!

በግርማ ሞገስ

የኢትዮጵያ ግብርና ከጊዜ ወደ ጊዜ በአፈር ማዳበሪያ ላይ ጥገኛ እየሆነ መጥቷል። አርሶ አደሩ በሰብል ልማት ላይ ማዳበሪያ የመጠቀሙ ጉዳይ እያደገ መምጣቱን ተከትሎ መሬቱ ያለአፈር ማዳበሪያ አያበቅልም። በዚህም የአርሶ አደሩ የግብርና ሥራ በአፈር ማዳበሪያ ላይ ጥገኛ እየሆነ መምጣቱ ይነገራል።

ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር ግብርናውን ማዘመንና የአፈር ማዳበሪያን በተገቢው ጊዜና ወቅት ለአርሶ አደሩ ማሰራጨት አስፈላጊ ነው። ማዳበሪያ በወቅቱና በሚፈለገው ልክ ለአርሶ አደሩ ማቅረብ ካልተቻለ መሬቱ ጾም እንዳደረ የሚቆጠርበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

‹encyclopedia of soil science› እንደሚያትተው፤ ማዳበሪያ ሰብሎች ለጥሩ እድገት የሚያስፈልጉትን ንጥረ ነገሮች ያቀርባል። አፈሩ በአነስተኛ የተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ ለረጅም ጊዜ የታረሰ ከሆነ፤ ማዳበሪያ መጠቀም ተጨማሪ እና የተሻለ ጥራት ያለው ምርት እንዲመረት ማረጋገጫ ነው።

የአፈር ማዳበሪያ መጠቀሙ አርሶ አደሮች አዲስ የእርሻ መሬት ፍለጋ የሚያደርጉትን ደን ምንጣሮ በመቀነስ ማዳበሪያን መጠቀም በአነስተኛ ቦታ ላይ ከፍተኛ ምርት እንዲገኝ ያደርጋል። ይህ ሲሆን የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ፈተና አይሆንም።

የግብርና ሚኒስቴር መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ ማዳበሪያ በቀጥታ የዕፅዋትን ዕድገት የሚያፋጥን የአፈር ውስጥ አልሚ ምግብ አቅርቦትን የሚጨምር ተፈጥሮአዊ ወይም ማዕድናዊ ንጥረ ነገር ነው። ማዳበሪያን በሰብል እርሻ ወይም ማሳ ላይ በመጨመር ምርታማነትን ማሳደግ ይቻላል።

እንደ ዩክሬን፤ ሩሲያና ሌሎች የአውሮፓ ሀገራት አሁን ለደረሱበት የዕድገት ደረጃ ዋና መሠረታቸው ግብርናን በአግባቡ በመጠቀማቸው ነው። ይህም የአፈር ማዳበሪያን በራሳቸው አቅም አምርተው ከራሳቸው አልፈውና ተርፈው ለአፍሪካ ሀገራት ከማቅረብ ባሻገር ስንዴም በርዳታ መልክ ይሰጣሉ።

ኢትዮጵያ የሀገራትን ተሞክሮ በመቀመር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ደፋ ቀና ማለት ከጀመረች ውላ አድራለች። ለዚህ እንደማሳያ የሚሆነው የአፈር ማዳበሪያን በወቅቱ በማቅረብ የአርሶ አደሩን ምርታማነት ማሳደግ ነው። ባለፈው በጀት ዓመት ከተከሰተው የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ክፍተት ትምህርት በመውሰድ በ2016/2017 የምርት ዘመን በተገቢ ጊዜ ለማቅረብ ግብርና ሚኒስቴር በዕቅድ እየሠራ ይገኛል።

በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ከጊዜ ወደ ጊዜ አርሶ አደሩ ማዳበሪያ ተጠቃሚ እየሆነ መምጣቱን ተከትሎ፣ ኢትዮጵያ የምታስገባው የአፈር ማዳበሪያ መጠን ከዓመት ዓመት እየጨመረ መምጣቱን የግብርና ሚኒስቴር መረጃዎች ያሳያሉ። የኢትዮጵያ አፈር ማዳበሪያ አጠቃቀም በ1960ዎቹ ውስጥ 35ሺ ኩንታል የነበረ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ከ17 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ደርሷል።

በ2008/2009 የምርት ዘመን የኢትዮጵያ አፈር ማዳበሪያ ዓመታዊ ፍጆታ አምስት ሚሊዮን 800 ሺ ኩንታል ሲሆን፣ ከአምስት ዓመት በኋላ በ2013/14 የምርት ዘመን 17 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ተጠቅማለች። ባለፉት አምስት የምርት ዓመታት ኢትዮጵያ የተጠቀመችው ማዳበሪያ በየዓመቱ እያደገ መጥቶ በአምስት ዓመት ውስጥ ከ11 ሚሊዮን ኩንታል በላይ እድገት አሳይቷል።

የአፈር ማዳበሪያ አጠቃቀም ፍላጎት ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ መጥቷል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ባለፈው 2015/2016 የምርት ዘመን ዩክሬንና ሩሲያ በገቡበት ግጭት ምክንያት የአፈር ማዳበሪያ ወቅቱን ጠብቆ ሀገር ውስጥ ባለመግባቱ እጥረት ተከስቶ ነበር። አንዳንድ ወገኖች ጉዳዩን የፖለቲካ አጀንዳ ለማድረግ የሄዱበት መንገድ የሚታወስ ነው   ።

‹ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ› እንዳይሆን መንግሥት ከባለፈው ስህተት ትምህርት በመውሰድ የ2016/17 የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት እና ስርጭትን ቀድሞ አቅዶ እየሠራ ነው። የግብርና ሚኒስቴር የባለፉት አምስት ወራትን የሥራ አፈጻጸም አስመልክቶ ከሳምንታት በፊት ለመገናኛ ብዙኃን በሰጠው መግለጫ እንዳስታወቀው ለ2016/17 ምርት ዘመን 23 ሚሊዮን 383ሺ 910 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ አቅዶ እየሠራ ነው።

**ወቅቱን የጠበቀ የአፈር** ማዳበሪያ አቅርቦት ሲኖር የአርሶ አደሩን ምርታማነት ይጨምራል

በመሆኑም በተፈቀደው የ930 ሚሊዮን ዶላር እና 71 ነጥብ 44 ቢሊዮን ብር 19 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ፈጽሞ ለማስገባት እየሠራ ነው። ይህም ባለፈው ዓመት ከተገዛው 12 ነጥብ 8 ሚሊዮን ኩንታል አንጻር ከፍተኛ ጭማሪ አለው።

እስከአሁን በድምሩ የ15 ነጥብ 8 ሚሊዮን ኩንታል ኤን ፒ ኤስ ዝርያ እና ዩሪያ የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ተፈፅሟል። ወደ ሀገር ውስጥ እየተጓጓዘ ያለ የማዳበሪያ መጠን እስከ ታኅሣሥ ዘጠኝ ቀን 2016 ዓ.ም በድምሩ ከ380ሺ ሜትሪክ ቶን በላይ  የአፈር ማዳበሪያ ጅቡቲ ወደብ ደርሷል።

ጅቡቲ ከደረሰው የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ እስከ ታኅሣሥ 9/2016 ዓ.ም ድረስ በድምሩ 255ሺ 206 ነጥብ 50 ሜትሪክ ቶን ወደ ሀገር ውስጥ ተጓጉዟል። በቀጣይ እስከ ጥር አጋማሽ ድረስ 262ሺ ሜትሪክ ቶን የጫኑ አራት መርከቦች ጅቡቲ ወደብ ይደርሳሉ። ወደ ኅብረት ሥራ ማኅበራት የተጓጓዘ የአፈር ማዳበሪያ መጠን 63ሺ 825 ነጥብ 48 ሜትሪክ ቶን ነው። ለመስኖ ልማት የሚውለው 20ሺ 639 ነጥብ 78 ሜትሪክ ቶን ለተጠቃሚው መሰራጨቱን የግብርና ሚኒስቴር አስታውቋል።

ከሰሞኑ የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ባወጣው መረጃ ደግሞ ለ2016/17 የምርት ዘመን ከውጭ ከተገዛው የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ እስከ ታኅሣሥ 20/2016 ዓ.ም ድረስ በዘጠኝ ዙሮች 4ሚሊዮን 380 ሺህ ኩንታል ጅቡቲ ወደብ  ደርሷል።

ከዚህ ውስጥ 3 ሚሊዮን 618 ሺህ 212 ኩንታል ማዳበሪያ ከወደብ ወደ ሀገር ውስጥ ተጓጉዞ በመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበር አማካኝነት ለአርሶ አደሮች እየተሰራጨ ነው። እስከ ጥር 10 ቀን 2016 ዓ.ም በሦስት መርከቦች ተጨማሪ ሁለት ሚሊዮን 90 ሺህ ኩንታል ኤን ፒ ኤስ፣ ኤን ፒ ኤስ ቦሮን እና ዩሪያ ማዳበሪያ ጅቡቲ ወደብ እንደሚደርስ የኮሚሽኑ መረጃ ያመላክታል።

ወቅቱን የጠበቀ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ሲኖር የአርሶ አደሩን ምርታማነት ይጨምራል። ስለሆነም የአፈር ማዳበሪያውን ማቅረብ ብቻ በቂ ባለመሆኑ ከፌዴራል እስከ ታችኛው የቀበሌ የኅብረት ሥራ ማኅበር ድረስ በተገቢው ሁኔታ ለአርሶ አደሩ መሰራጨቱን  መከታተል አስፈላጊ ነው።

ይህ ሲሆን ገበሬው ከቅሬታ ነጻ ከመሆኑም ባሻገር በአላስፈላጊ መንገድ ሰው ሠራሽ የአፈር ማዳበሪያ እጥረት እንዳይከሰት የሚረዳ መሆኑ ልክ እንደ አቅርቦቱ ሁሉ ከትትልና ቁጥጥሩም ሊጠናከር ይገባል። በተጨማሪም ዓለም ተለዋዋጭ በሆነ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ እንደመሆኑ መጠን የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ዘላቂ የሆነ መፍትሔ እንዲሰጠው በራስ አቅም የሚመረትበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተገቢ ነው።

# ተጠየቅ

## “የኢትዮጵያ የኅብረት ሥራ ማህበራት የእድሜያቸውን እና የብዛታቸውን ያህል እየሠሩ አይደለም”

*- ዶክተር ጌታቸው መለሰ*
*የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር*

ሞገስ ተስፋ እና ሙሉቀን ታደገ

በኢትዮጵያ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከተቋቋሙ ረጅም ታሪክ አስቆጥረዋል:: በዚህም ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ቀዳሚ ከሚባሉ ሀገራት ተርታ ትጠቀሳለች። በሀገሪቱ ዘመናዊ የህብረት ሥራ ማህበራት በቅድመ አብዮት ጊዜ በ1953 ዓ.ም የገበሬዎች እርሻ ድንጋጌ በማውጣት የተጀመረ ሲሆን፤ በደርግ ዘመንም ሆነ ከደርግ ሥርዓት በኋላ ዓለም አቀፍ መርሆችን በማካተትና ማሻሻያ በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራት ድንጋጌዎችና አዋጆች ወጥተው ተግባራዊ ለማድረግ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይቷል።

ይሁን እንጂ ህብረት ሥራ ማህበራት በእድሜ ደረጃ ከ60 ዓመት በላይ ቢያስቆጥሩም፤ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከማሳደግ አኳያ ያላቸው አስተዋጽኦ ከዚህ ግባ የሚባል አይደለም:: ለዚህ ደግሞ በየሥርዓቱ የነበረው የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴ የተለያየ መልክ እየያዘ እና መንግሥታትም የፖለቲካ መሳሪያ አድርገው ይጠቀሙባቸው ስለነበር ሲሆን፤ ይሄም ህብረት ሥራ ማህበራቱ መድረስ በነበረባቸው የእድገት ደረጃ ላይ መድረስ እንዳይችሉ አድርጓቸዋል:: በዚህም በህብረት ሥራ ማህበራት በኩል ከኢትዮጵያ ልምድ የወሰደችው ጎረቤት ሀገር ኬንያን ያህል እንኳን ልትጠቀምባቸው አልቻለችም::

ለምሳሌ፣ ከኢትዮጵያ ልምድ የወሰደችው ኬንያ፣ አሁን ላይ 45 በመቶ የሚሆነውን የሀገሪቱን ጥቅል ምርት የሚሸፈነው በህብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት ነው :: የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ማህበራት ግን ከዚህ ግባ የሚባሉ አይደሉም:: እናም የህብረት ሥራ ማህበራት እስካሁን በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚጫወቱት ሚናቸው ለምን አላደገም? ካለፈው ስህተታቸው ተምረው ውጤታማ እንዲሆኑስ አሁን ላይ ምን እየተሰራ ነው? በሚሉና ሌሎች ጉዳዮች ላይ በማተኮር፣ ከፌዴራል ህብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ጌታቸው መለሰ ጋር ቆይታ አድርገናል:: መልካም ምንባብ::



**አዲስ ዘመን፡- የተቋሙ ስያሜ ከኤጀንሲ ወደ ኮሚሽን መቀየሩ በሚያከናውነው ተግባር ላይ የሚኖረው ፋይዳ ምንድን ነው?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** የአሁኑ የህብረት ሥራ ኮሚሽን እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ይባል ነበር:: ይሄም ኢህአዴግ ከገባ በኋላ በአዲስ መልክ በመደራጀቱ ነው:: ሆኖም ከዛ በፊት በ1994 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 274/ 94 መሰረት ሲደራጅ ስያሜው ኮሚሽን ነበር:: ይሁን እንጂ በሂደት የተለያዩ ለውጦች ሲመጡና የተለያዩ አደረጃጀቶች ሲፈጠሩ ኤጀንሲ የመሆን ዕድል አጋጥሞት ነበር:: በ2014 ዓ.ም ግን በድጋሚ የአስፈጻሚ አካሉን ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት የኢትዮጵያ ህብረት ስራ ኤጀንሲ ወደ ኮሚሽን እንዲያድግ ተደጓል::

ወደ ጥያቄው ስመለስ እያንዳንዱን መዋቅራዊ አደረጃጀት (ለምሳሌ፣ ኤጀንሲ፤ ኮሚሽንና ሚኒስቴር) ደግሞ የየራሳቸው ደረጃ አላቸው:: የእኛም ተቋም ከኤጀንሲ ወደ ኮሚሽን ከፍ ሲል በሰው ኃይል አደረጃጀት ያድጋል:: በዚህ አግባብም አስፈላጊው ሥራ ተከናውኖ ተግባርና ኃላፊነቱ የተሻለ እንዲያድግ ተደርጓል::

ከዚህ በተጓዳኝ ኮሚሽን መሆኑ፣ ፖሊሲን በራሱ አርቀቆ ለሚኒስቴሮች ምክር ቤት የማቅረብ ስልጣን ይኖረዋል:: በዚህ መሰረት የራሱን ፖሊሲ ለማርቀቅ የፖሊሲ ጥናቶን ማካሄድ ተችሏል:: በዚህ በጀት ዓመት የመደበኛው ስራ እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት በኮሚሽኑ ትልቅ ለውጥ መምጣት እንዳለበት ታስቦ በእቅድ እየተሰራ ነው::

በተለይ በሀራችን የህብረት ሥራ ማህበራት ከተቋቋሙ ወደ 63 ዓመታትን አስቆጥረዋል:: ለምሳሌ፣ በ1953 ዓ.ም የመሬት አዋጅ ድንጋጌ በሚል እንዲቋቋሙ ተደርገዋል:: ይህም ትልቅ ዕድሜ ሲሆን፤ አንዳንድ ተቋማት ከዚህ በኋላ ተቋቁመው ትልቅ ደረጃ ደርሰዋል:: ነገር ግን የህብረት ሥራ ማህበራት ትልቅ ዕድሜ ቢያስቆጥሩም ዕድሜያቸውን ያህል መስራት አልቻሉም:: በመሆኑም የተፈጠረውን እድል ተጠቅሞ ይሄን ለመቀየር እየተሰራ ይገኛል::

**አዲስ ዘመን፡- ህብረት ሥራ ማህበራቱ የዕድሜያቸውን ያህል እንዳይሰሩ፣ እንዳያድጉና እንዳይዘምኑ የሆኑበት ምክንያት ምንድን ነው?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** የህብረት ስራ ማህበራት ስርዓቶች በተቀያየሩ ቁጥር የስርዓቱ ፖለቲካ ማስፈጸሚያ ሆነው ሲያገለግሉ ነበር:: ለምሳሌ፣ በንጉሱ ጊዜ ከማህበራት ጋር ተያይዞ ራሱን የቻለ አመለካከት ነበር:: ደርግ ሲመጣ ደግሞ የራሱን የሶሻሊስት አስተሳሰብን እንዲያራምዱለት የገበሬዎች የህብረት ስራ ማህበር በሚል በመቋቋሙ የስርዓት አራማጅ አደረጋቸው:: በዚህም ህብረተሰቡ ስለህብረት ስራ ማህበራት የተዛባ አመለካከት እንዲኖረው አድርጎታል::

በኢህአዴግ ጊዜ ለውጥ ሲደረግ ማህበራቱ የመጥፋት ሁኔታዎች አጋጥሟቸው ነበር:: በአጠቃላይ መንግሥት በተቀያየረ ቁጥር ከተቋቋሙለት ዓላማቸው በማፈንገጥ የየሥርዓቱ ማስፈጸሚያ ሆነው ሲያገለግሉ ነበር:: በዚህም የሀገራችን የህብረት ሥራ ማህበራት ካስቆጠሩት እድሜ አንጻር የሚጠበቅባቸውን ውጤት ሊያመጡ አልቻሉም::

**አዲስ ዘመን፡- የህብረት ሥራ ማህበራት በዕድሜያቸው ልክ ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደረጋቸው የሥርዓት ማስፈጸሚያ መሆናቸው ብቻ ነው? ወይስ ሌሎች ምክንያቶች አሉ?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** ቁልፉ ችግር የነበረው የአስተሳሰብ ነው:: ይህ ሲባል ከሥርዓት ለውጥ ጋር የሚመጣ የተለያየ አስተሳሰብ ስላለ ማህበራቱን ወደ ኋላና ወደፊት ሲጎትታቸው ይስተዋላል:: የመንግሥት ሥርዓት በተቀያየረ ቁጥር አብሮ የሥርዓቱን አስተሳሰብ የማራመድ ነገር ነበር::

ይህ እንዳለ ሆኖ በራሳቸው የውስጥ አሰራርም ደካማ ናቸው:: ብዙ ቁጥር የሚሸፍኑት በግብርናው ዘርፍ የተቋቋሙ ማህበራት ናቸው:: እነዚህ ማህበራት የሚመሩት ባልተማረ የሰው ኃይል እና አርሶ አደሮች ነው:: እስካሁን ድረስም በግብርናው ዙሪያ የሚገኙ ማህበራት የሚመሩት በአርሶ አደር ነው:: ሆኖም የግብርና ስራውን በሚፈለገው ልክ ለማንቀሳቀስ ማህበራቱን በተማረ የሰው ኃይል መምራት ያስፈልጋል:: ነገር ግን በኢትዮጵያ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ከዚህ የተለየ ነው::

ነገር ግን የህብረት ሥራ ማህበራት ማለት የቢዝነስ ማንቀሳቀሻ አካልና የኢኮኖሚ ተቋም ናቸው:: የኢኮኖሚ ተቋምን ደግሞ በደንብ አስቦና አቅዶ መምራት ይጠይቃል:: ነገር ግን በእኛ ሀገር ማህበራት በደንብ አስቦና አቅዶ የመምራት ችግሮች ይስተዋላሉ::

በተጨማሪም በእኛ ሀገር ማህበራት እንደ አንድ ትልቅ ክፍተት የሚታየው በስራቸው የሚቀጠሩ ሥራ አስኪያጆች ከማህበሩ ውጪ ያሉ መሆናቸው ነው:: ይህ ተናቦ በመስራት ሂደት ላይ ችግር ፈጥሯል::

በማህበራቱ ላይ የሚካሄድን ምዝበራ በአግባቡ ከመቆጣጠር አንጻር ክፍተቶች መኖሩ ሌላው በሀገራችን የሚገኙ ማህበራት ከእድሜአቸው አንጻር በስራቸው ውጤታማ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል:: ከሰራተኛው እስከ የቦርድ አመራሩ በገባው ቃል መሰረት ውጤት በማምጣት ረገድ የሚጎድል ነገር አለ::

ማህበራቱ በቢዝነስ ውስጥ ያላቸው ፍላጎት አነሳ በመሆኑ፣ የአባላቱን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ባለመቻላቸው፤ አባሉም የእኔ ነው ብሎ አምኖ ተቀብሎ በመደገፍና በመስራት በኩል ችግሮች እንዲፈጠሩ አድርጓል:: በተለይም የፍላጎት ወይም መተማመን አለመኖር በመፈጠሩ ሁሉም በገባው ቃል መሰረት እንዳይሰራ አድርጓል:: በቢዝነስ ውስጥ ደግሞ መተማመንና ለስራው ፍላጎት ከሌለ፤ በአባላት ውስጥ ተጠቃሚነት ካልተረጋገጠ ውጤት ሊገኝ አይችልም::

ከዚህም ባሻገር የመንግሥት መዋቅር ከላይ እስከ ታች ድረስ ወጥ ያለመሆን ችግር ማህበራት በእድሜቻቸው ልክ መስራት እና ማድግ እንዳይችሉ አድርጓቸዋል:: ምክንያቱም፣ ከኮሚሽን ጀምሮ እስከ ህብረት ስራ ማህበራት ድረስ ማህበራትን የሚደግፉበት ወጥ የሆነ አሰራር የለም:: ስለዚህ መዋቅራዊ ችግር ሌላኛው በሀገራችን ለሚገኙ ማህበራት ፈታኝ ሁኔታ ነው::

ከአደረጃጀቱ አኳያ ብንመለከት የማህበራቱ በየአቅጣጫው የተበተነ ነበር:: አዋጅ በቁጥር 274/94 ከወጣ በኋላ ግን በተሻለ መልኩ አደረጃጀታቸው እንዲሰበሰብ ተደርጓል:: ይሁን እንጂ አሁን ላይ እነዚህን ሁሉ ችግሮች በሪፎርም መመለስ አለበት ተብሎ እየተሰራ ነው::

**አዲስ ዘመን ፡- ማህበራቱ በለውጥ ጎዳና ተጉዘው በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚኖራቸውን ሚና ለማሳደግ ኮሚሽኑ ምን እየሰራ ነው?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** ማህበራቱ በለውጥ ጎዳና ተጉዘው በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚኖራቸውን ሚና ማሳደግ እንዲችሉ ለማድረግ በአሁኑ ሰዓት ኮሚሽኑ በርካታ የሪፎርም ስራዎች እየተሰራ ነው:: ለዚህ ሥራችን ከኢትዮጵያ ልምድ ወስዳ ውጤታማ የሆነችውን ኬንያን መመልከት በቂ ቁጭትና መነሳሳትን የሚሰጠን ነው:: ምክንያቱም፣ ኬንያ የህብረት ሥራ ልምድን የወሰደችው ከኢትዮጵያ ነው:: በደርግ ጊዜ ከተቋቋሙት እንደ አጋርፋና አርዳይታን የመሳሰሉ የማሰልጠኛ ተቋማት ሙያተኞች ወደ ኬንያ እየተላኩ ስልጠና እንዲሰጡ ተደርጓል::

በእነዚህ ባለሙያዎች ለኬንያውየን የተሰጠው ስልጠናም በኬንያ የሚገኙ የህብረት ሥራ ማህበራትን በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ትልቅ ሚና እንዲጫወቱ አስችሏቸዋል:: በዚህም አሁን ላይ ለኬንያ የሀገር ውስጥ ጠቅላላ የኢኮኖሚ ዕድገት 45 በመቶ አስተዋጽኦ አላቸው:: ምክንያቱም፣ 76 በመቶ የሚሆነው የወተት ምርት፤ 90 በመቶ የሚሆነው የጥጥ ምርት በህብረት ስራ ማህበር የሚቀርብ ነው:: የቤት ልማት ሲታይ አብዛኛው በሚባል ደረጃ የህብረት ስራ ማህበራት የሚገነቡት ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የታክሲ አገልግሎት የሚሰጡት የህብረት ስራ ማህበራት ናቸው:: የራሳቸውም ባንክ አላቸው:: በአጠቃላይ ሲታይ በኬንያ የህብረት ስራ ማህበራት በኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው::

ከዚህ አንጻር ከኢትዮጵያ ህብረት ሥራ መፈጠር በኋላ የተመሰረቱት የኬንያ የህብረት ሥራ ማህበራት

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

# ተጠየቅ

## “የኢትዮጵያ የኅብረት ሥራ ማህበራት የእድሜያቸውን...

ከገጽ 6 የዞረ

የደረሱበት ደረጃ ስንመለከት እኛ የት ነን? ብለን እንድንጠይቅ የሚያደርግ ነው:: ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያ 110 ሺ መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት፤ 403 ዩኔኖች፤ አምስት ፌዴሬሽኖች አሉ:: የሁሉም ህብረት ስራ ማህበራት ካፒታል ሲሰላ 59 ቢሊዮን ብር ነው:: አንድ ቢሊዮን ዶላር ገደማ እንደማለት ነው:: በኬንያ ግን አምስት ሺ ኅብረት ስራ ማኅበራት ስምንት መቶ ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ካፒታል አላቸው:: ይህ ምን ያህል ካፒታላቸው እንዳደገ የሚያሳይ ነው:: የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ማህበራት ግን ከስምና ቁጥር ውጭ እዚህ ግባ የሚባል ውጤት የላቸውም::

**አዲስ ዘመን፡- የህብረት ሥራ ማህበራት በየጊዜው ከሚፈጠርባቸው መንግሥታዊ ጣልቃ ገብነት ነጻ እንዲሆኑ፣ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል ምን ታስቧል?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** የህብረት ሥራ ማህበራት አጠቃላይ ከመንግሥት ተፅዕኖ ነጻ ይወጣሉ ማለት ትክክል አይደለም:: ምክንያቱም የሚያገናኛቸው አሰራር ይኖራል:: በተቃራኒው ደግሞ የማያገናኛቸው ይኖራል:: ዋናው ነገር ሚናቸውን በውል በመለየት መደጋገፍ ነው:: እስካሁን ባለው ሂደት መንግስት የኦዲት፤ የኢንስፔክሽን፤ የፋይናንስ መሰል ሙያዊ ድጋፍ እየሰጠ ነው::

ጣልቃ መግባት ሲባል ግን በህብረት ስራ ማህበራት የዕለት ተዕለት ስራቸው ላይ እየገባ መወሰን የለበትም ነው:: ወይም ማህበራቱ ያመረቱት ምርት “በዚህን ያህል ዋጋ ሽጡ” ብሎ ዋጋ መቁረጥ እና በቦርድ ውሳኔ ላይ ጣልቃ ገብቶ መወሰን የለበትም ለማለት ነው:: በአጠቃላይ የፖለቲካ ማስፈጸሚያ መሳሪያ መሆን የለባቸውም:: ነገር ግን ድጋፍ ማድረግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል::

አሁን ላይ እየተሰራ ያለው ሪፎርም ማህበራትን ነጻ ከማድረጉም ባለፈ፣ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲመሩ መደገፍ ባለባቸው ደረጃ ልክ እንዲደገፉ አሰራር ለማበጀት የሚረዳ ነው:: ለዚህም መንግስት ፖለተካዊ ቁርጠኝነት ጭምር ኖሮት እየተሰራ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ሪፎርሙን ውጤታማ ከማድረግ አኳያ ስራው እንዴትና በማን እየተመራ ነው?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** የሪፎርም ስራው በግብርና ሚኒስትሩ ዶክተር ግርማ አመንቴ የሚሰበሰቡት አብይ ኮሚቴ ተቋቁሞ እየተሰራ ሲሆን፤ የቴክኒክ ኮሚቴው ደግሞ በህብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ሽሰማ ገብረ ስላሴ የሚመራ ነው:: ይህም እስከ ታችኛው የመዋቅርና የአደረጃጀት እርከን የሚወርድ ነው::

በዚህም እስካሁን የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር የህብረት ሥራ ማህበራት ሪፎርሙ የሚሰጠው ጥቅም፤ የነበሩ ችግሮች ምን ምን እንደሆኑ፤ እንዴት መቀረፍ እንዳለባቸው የማስገንዘብ ስራ ሲሰራ ቆይቷል:: እንደ ሀገርም የህብረት ሥራ የሪፈርም ንቅናቄ ተጀምሮ የተለያሰዩ ስራዎችን እየሰራን ነው::

**አዲስ ዘመን፡- የሪፎርም ስራው መቼ ይጠናቀቃል? ምን ምን ጉዳዮችንስ ይመልሳል?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** የሪፎርም ስራው ሁለት መልክ አለው:: በዚህ አመት የታቀዱ አዋጅና ደንብ የማያስፈልጋቸው እስካሁን መስራት ሲገባን ያልሰራናቸውን ተግባራትን መስራት ቅድሚያ የተሰጠው ነው:: ከዚህ ባሻገር ግን የሪፎርም ስራው ከዓመት በላይ ጊዜ ሊወስድ ይችላል:: ምክንያቱም በግብርና መር ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ድጋፍ አማካኝነት የዓለም ባንክ ድጋፍ የሚያደርገው አማካሪ ተቀጥሮ በጥልቀት የፖሊሲ ስራዎችን የሚመለከት ጥናት እየተሰራ ነው::

ኮሚሽኑም በዓመት ውስጥ የሚሰራቸው በዋናነት አምስት ተግባራቶች አሉት:: የመጀመሪያው ማህበራቱ ቁጥራቸው ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ሀብታቸውና ጉልበታው/አቅማቸው ተበታትኗል:: ከዚህ አንጻር

> የህብረት ሥራ ማህበራት የራሳቸውን አቅም ከገነቡ፣ የፋይናንስ ችግር ከተቀረፈላቸው ደላላ የሚባለው ነገር ላይመጣ ይችላል

በአንድ ሥራ ክልል ውስጥ አንድ ተመሳሳይ የህብረት ሥራ ማህበራት ካለ ሌላ ተመሳሳይ የህብረት ሥራ ማህበራት መፈጠር እንደሌለበት በአዋጁ ተቀምጧል:: ነገር ግን የኢትዮጵያ የቀበሌዎች ብዛት 17 ሺ ሆኖ እያለ 110 ሺ የሚደርሱ የህብረት ሥራ ማህበራት ተፈጥረዋል::

የግብርና ማህበራት ብቻ ሲታዩ ወደ 28 ሺ ይደርሳሉ:: ስለዚህ አንዱ ስራ አዋጁን በትክል ተግባራዊ ማድረግ ነው:: ይህ ሲደረግ የተበታተኑትን ማህበራት ሰብሰብ በማድረግ ጉልበታቸውና ካፒታላቸው እንዲጠነክር ማድርግ ነው :: ይህም የፋይናንስ ችግራቸውን ሌላ ሳይጠብቁ ሊቀርፉ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል:: ስለዚህ ማህበራትን የማዋሃድ ስራ ለመስራት በዕቅድ ተይዟል::

ሁለተኛው፣ የህብረት ሥራ ማህበራት በአርሶ አደርና ባልተማረ የሰው ኃይል ስለሚመሩ ቦርዱ በባሙያ መደገፍ አለበት ተብሎ የባለሙያዎች አማካሪ ቦርድ (professional advisory board) የሚል እየተተገበረ ነው:: ይህ ሲሆን ቴክኒካል ክፍተቶች ይቀረፋሉ:: ሶስተኛው፣ የህብረት ሥራ ማህበራት ችግር ፋናንስ ነው:: ይን ችግራቸውን ለመፍታት እየተሰራ ነው:: በሀገራችን የሚገኙ የህብረት ሥራ ማህበራት ከፍተኛ የፋናንስ ችግር ስላለባቸው ብዙ ጊዜ በተለይም ምርት በሚሰበሰብበት ወቅት በቀጥታ ምርት ከአርሶ አደሩ በመግዛት በተፈለገው ልክ ገበያውን ሲያረጋጉት አይታዩም :: ስለሆነም ይህን ችግር ለመቅረፍ የራሳቸውን ባንክ ለማቋቋም የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ ነው::

ሌላው ችግር፣ የህብረት ሥራ ማህበራቱን ሊደግፍ እና ሊወክል የሚል ራሱን የቻለ ተቋም አለመኖሩ ነው:: በሀገራችን ህብረት ስራ ማህበራት፤ ዩኔኖችና የፌዴሬሽን አደረጃጀቶች አሉ:: ነገር ግን እነዚህን ሰብሰብ አድርጎ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚወክል ተቋም የለም:: በምርምር፤ በስልጠና፤ በበጀት፤ በኦዲትና በሌሎች ስራዎቸ ሊደግፉቸው የሚችል ብሔራዊ ተቋም የለም::

ይህ ተቋም ልክ እንደመንግሥት “አከት” የሚያደርግ ነው:: ለምሳሌ፣ የወጣቶች ሊግ የሚባል አለ:: ይህ ወጣቶች ሊግ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጣቶችን ይወክላል:: ህብረት ሥራ ማህበራት ላይ ስንመጣ ግን የህብረት ሥራ ማህበራትን የሚወክል የልም:: አርሶ አደሩንም እንዲሁ የሚወክል ተቋም የለም:: በዚህ ሰዓት አርሶ አደርን ሊወክሉ የሚችሉ ህብረት ሥራ ማህበራት ናቸው :: እነሱን የሚወክል በፌዴራል ደረጃ ሊግ መኖር ነበረበት :: አሁን ላይ ኮሚሽኑ ብቻ ነው እኔ ነኝ የማቀውቅላችሁ እያለ እየሰራ ነው :: በሌሎች ሀገራት ላይ ግን ማህበራትን እና አርሶአደሮችን ሊወክል የሚችል ተቋም በስፋት አለ:: በመሆኑም ይህን አይነት ወካይ ተቋም ለመገንባት እየሰራን ነው ::

ሌላኛው፣ ኦዲቲንግ ነው:: 106 ሺህ ማህበራትን በአንድ ዓመት ኦዲት ማድረግ አንችልም :: በኦዲት አሰራር መሰረት በዓመት አንድ ድርጅት በየአመቱ ኦዲት መደረግ አለበት :: ኦዲት ካልተደረገ ያ ማህበር ጤናማ ሊሆን አይችልም:: አርሶ አደሩ ደግሞ ወደ ህብረርት ስራ ማህበሩ ያለችውን ገንዘብ ይዞ የሚመጣው መንግሥትን አምኖ ነው :: በየአመቱ ኦዲት መደረግ ካልተቻለ እንዴት ነው የአርሶአደሩን ሀብት መጠበቅ የሚቻለው? ምክንያቱም ከላይ እስከታች ድረስ ኦዲት የማድረግ የአቅም ውስንነት አለ:: ስለዚህ እኛ የምንወክለው ማህበር ኦዲት መደረግ አለበት ብልን መመሪያ አዘጋጅተናል:: ይህ መመሪያ የሪፎርሙ አካል ነበር :: አሁን ላይ በፍትህ ሚኒስቴር ጸድቆ መጥቶልናል::

**አዲስ ዘመን ፡- የኦዲት ችግር ከነበረ 106 ሺህ ማህብራት ባሉበት ሀገር ከዚህ በፊት የነበሩ የኢዲት ሥራ አፈጻጸማችሁ ምን ይመስል ነበር?**

**ዶክትር ጌታቸው፡-** አንዱ የእኛ አፈጻጸም ችግራችን የኦዲት ሽፋን ነው :: ካሉን አጠቃላይ ማህበራት አንጻር ሲታ የኦዲት ሽፋናችን ከ25 እስከ 30 በመቶ በልጦ አያውቅም:: በዓመት ውስጥ ኦዲት እናደርጋለን ብልን ከያዝነው እቅድ አንጻር ግን እስከ 85 በመቶ እንደርሳለን:: ነገር ግን በየዓመቱ ሁሉም መደረግ ነበረበት:: ከዚህ አንጻር ሲታይ የኦዲት ሽፋናችን ዝቅተኛ ነው:: ይህ ደግሞ የሀብት ብክነት እያመጣ ነው:: ማህበራትም ምዝበራ ውስጥ እየገቡ ነው::

**አዲስ ዘመን ፡- አምራቾቹን ከዩኒየናች ጋር ከማገናኘት አንጻር ያሉ ጥንካሬዎች እና ውስንነቶች ምንድን ናቸው?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** እነኚህ ማህበራት የተወሰነም ቢሆን ካፒታል አላቸው:: በዚች ካፒታላቸው ለገጠሩ ማህበረሰብ የፋይናንስ ምንጭ ሆነው እያገለገሉ ያሉት የህብረት ሥራ ማህበራት አሉ:: በተለይ ባንክ ባልደረሰበት አካባቢ የህብረት ስራ ማህበራት የህዝባችንን ችግር እየቀረፉ ናቸው:: በስራ አድል ፈጠራም ቢሆን የህብረት ስራ ማህበራት የጎላ ድርሻ አላቸው ::

ለምሳሌ፣ የዘመናዊ ታክሲ አግልግሎት በአዲስ አባባ ብንመለከት በስፋት ገንዘብ እየተሰጠ ያለው አዋጭ የገንዘብ ቁጠባ ማህበር ነው:: አሁን በቅርብ አሚጎስ ላዳ ታክሲዎችን ወደ ዘመናዊ ታክሲ እየቀየረ ነው::

በከፍተኛ ደረጃ ወደ አግሮ ፕሮስሲንግ ስራሳ የገቡም አሉ:: 36 የሚሆኑ የህብረት ስራ ማህበራት እሴት በመጨመር ወደ ከፍተኛ አግሮ ፕሮሰሲንግ ስራዎች ገብተዋል:: ከዚህ በተጨማሪ 98 በመቶ የሚሆነው የግብርና ግብዓት የሚሰራጨው በህብረት ስራ ማህበራት ነው::

የሁላችንም ኩራት ከሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩ የህብረት ስራ ማህበራት አሉ:: የሪፎርሙ ዋና አላማም በሀገራችን የሚገኙ ሁሉም ማህበራት በእነዚህ ማህበራት ልክ እንዲደሰሩ ማድረግ ነው ::

አሁን ላይ የህብረት ስራ ማህበራት የሀር ውስጥ ግብይት ከ9 እስከ 18 በመቶ ነው:: ይህ ማለት ከ80 በመቶ በላይ የሀገሪቱ ግብይት ከህብረት ሥራ ማህበራት ውጭ ይካሄዳል ማለት ነው:: የህብረት ሥራ ማህበራትን የገበያ ድርሻ ማሳደግ ካልተቻለ በሚፈለገው ልክ ገበያውን ማረጋጋት አይቻልም:: የሪፎርሙ አንዱ ዓላማም የማህበራቱን የገበያ ድርሻ ማሳድግ ነው:: ምክንያቱም የገበያ ድርሻቸው ካላደገ ገበያውን ማረጋጋት አይችሉም ::

በሌሎች ሀገራት ላይ ዋጋን የሚተምኑት የህብረት ሥራ ማህበራት ናቸው :: በዚህም ሌላው የነጋዴ ክፍል ዋጋ ተቀባይ ነው:: በእኛ ሀገር ግን ዋጋ ሰጪ ሳይሆኑ ከነጋዴው ዋጋ ተቀባይ ናቸው:: ይህ ደግሞ በታሰበው ልክ በሀገሪቱ የሚስተዋለውን የኑሮ ውድነት ማረጋጋት አያስችላቸውም::

**አዲስ ዘመን ፡- ዩኒየኖችን እና አርሶ አደሮችን በቀጥታ እንዲገናኙ በማድረግ በሀገራችን የሚስተዋለውን ሰው ሰራሽ የኑሮ ውድነት ለመቀነስ በሪፎርሙ ምን ታስቧል?**

**ዶክትር ጌታቸው፡-** ይህ የንግድ ሥርዓት ነው :: አንዳንዴ በንግድ ሥራ ሥርዓቱ ማህበራት በራሳቸው የሚሰሯቸው ስራዎች አሉ:: የህብረት ሥራ ማህበራት የራሳቸውን አቅም ከገነቡ፣ የፋይናስ ችግር ከተቀረፈላቸው ደላላ የሚባለው ነገር ላይመጣ ይችላል:: የህብረት ስራ ማህበራቶች በተፈለገው በወቅቱ ገንዘብ በመያዝ የአርሶ አደሮችን ምርት መግዛት በማይችሉበት ጊዜ ደላሎች በቀላሉ ወደ ገበያው ይገባሉ:: ይህ ደግሞ ላልተገባ የዋጋ ንረት ይዳርጋል::

ብዙ ጊዜ መንግሥት ለህብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጣቸው የተዘዋዋሪ ፈንድ ድጋፍ ዘግይቶ ነው የሚደርሰው:: ገንዘቡ ከዘገየ ደግሞ ምርቱ በደላላ ስለሚወሰድ ምርት የለም ማለት ነው:: ስለሆነም በሪፎርሙ የአርሶ አደሮችን እና ዩኔኖችን በቀጥታ በማገናኘት ደላሎችን እና ያልተገባ የሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ለመከላካል የህብረት ስራ ማህበራትን የፋይናንስ አቅም የማጎልበት ሥራ እየሰራን ነው::

**አዲስ ዘመን ፡- ተቋሙ የራሱን ተቋም ስመገንባት እና ራሱን ስማስተዋወቅ ምን እየሰራ ነው?**

**ዶክተር ጌታቸው ፡-** ተቋም ማለት ህንጻው ከሆነ ህንጻ የለንም :: ግን መዋቅር ያለው ተቋም አለን ::

ራስን ከማስተዋወቅ አንጻር ሚዲያ እና ኮሙኒኬሽን ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ:: ስለሆነም በሚዲያ እና ኮሙኒኬሽን ተጠቅመን የህብረት ስራ ኮሚሽን ምን የሚሰራ ነው የሚለውን ለማስተዋወቅ ከፍተኛን ስራዎች እየተሰሩ ነው ::

አሁን ላይ ኮሚሽኑ “ብራንዲግ” ላይ እየሰራ ነው:: የተቋሙ ሎጎ ኮፕ ( coop ) ነው:: ነገር ግን ቀለሙ ኢንተርናሽናል ኮፕረቲቭ አልያንስ ነው:: እሱን ወደ ፊት የራሳችን ሎጎ ምን መሆን አለበት የሚለውን አብረን ከሪፎርሙ ጋር እየሰራን ነው::

**አዲስ ዘመን ፡- የተክኖሎጂ ሽግግር ጋር በተያያዘ በሪፎርሙ ምን ታቅዷል?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** አንዱ የህብረት ሥራ ማህበራት ችግር ቴክኖሎጂን አለመጠቀም ነው:: በሪፎርሙ ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ ለማድርግ ካቷል:: የህብረት ሥራ ማህበራት ፋይናሽያል ተቋም እንደመሆናቸው የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ መሆን አለባቸው:: የፋይናሽያል አሰራራቸው በቴክኖሎጂ መደገፍ አለበት:: አሁን ላይ አንዳንድ የብድር ተቋማት የራሳቸውን ሰርቨር ኖሯቸው የባንክ አሰራር እንዲጠቀሙ የማድረግ ሥራ እየተሰራ ነው ::

**አዲስ ዘመን ፡- ለቃለ መጠየቅ ፈቃደኛ ሆነው ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን::**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

# ማኅበራት በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚኖራቸውን ሚና ለማሳደግ ሪፎርም እየተሠራ ነው

**ሞገስ ተስፋና ሙሉቀን ታደገ**

አዲስ አበባ፡- የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከነበሩበት ችግር ወጥተው በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚኖራቸውን ሚና ለማሳደግ የሪፎርም ሥራ እየሠራ መሆኑን የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌታቸው መለሰ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ኮሚሽነሩ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የኅብረት ሥራ ከተቋቋሙ በርካታ ዓመታትን ቢያስቆጥሩም በዕድሜያቸው ልክ ዘምነው በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጉልህ ሚና እየተጫወቱ አይደለም፡፡ ለዚህ ደግሞ ማኅበራቱ ሥርዓቶች በተቀያየሩ ቁጥር የሥርዓቱ የፖለቲካ ማስፈጸሚያ መሆናቸው አንዱ ምክንያት ነው፡፡

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ የኅብረት ሥራ ማኅበራት በቁጥራቸው ልክ ኢኮኖሚው ላይ ያላቸው ሚና ላለማደግ ቁልፉ ችግር የነበረው የአስተሳሰብ ነው፡፡ ይህ ሲባል ከሥርዓቱ ለውጥ ጋር የሚመጣ የተለያየ አስተሳሰብ ስላለ ማኅበራቱን ወደ ኋላና ወደፊት ሲጎትታቸው ተስተውሏል፡፡ ብዙ ቁጥር የሚሸፍኑት ማኅበራት በግብርናው ዘርፍ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ እነዚህ ማኅበራት የሚመሩት ባልተማረ የሰው ኃይል እና በአርሶ አደሮች ነው፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ ማኅበራትን በደንብ አስቦና አቅዶ የመምራት ችግሮች ነበሩ ብለዋል፡፡

ማኅበራቱ በቢዝነስ ውስጥ ያላቸው ፍላጎት አናሳ በመሆኑና የአባላቱን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ባለመቻላቸው፣ አባሉም የእኔ ነው ብሎ አምኖ ተቀብሎ በመደገፍና በመሥራት በኩል ችግሮች እንዲፈጠሩ አድርጓል፡፡ የፍላጎት ወይም መተማመን አለመኖር በመፈጠሩ ሁሉም በገባው ቃል መሠረት እንዳይሠራ አድርጓል ብለዋል፡፡

ጌታቸው (ዶ/ር)፤ ማኅበራቱ በለውጥ ጎዳና ተጉዘው በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚኖራቸውን ሚና ማሳደግ እንዲችሉ ኮሚሽኑ የሪፎርም ሥራዎችን እየሠራ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ የሪፎርም ሥራውም በግብርና ሚኒስትሩ ዶክተር ግርማ አመንቴ ሰብሳቢነት ዐቢይ ኮሚቴ ተቋቁሞ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር የቴክኒክ ኮሚቴው በኅብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ሽሰማ ገብረ ሥላሴ የሚመራ ሲሆን ይህም እስከ ታችኛው የመዋቅርና የአደረጃጀት እርከን የሚወርድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እስካሁን የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሪፎርሙ የሚሰጠው ጥቅም፣ የነበሩ ችግሮች ምን ምን እንደሆኑ፤ እንዴት መቀረፍ እንዳለባቸው የማስገንዘብ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል ያሉት ኮሚሽነሩ፤ እንደ ሀገርም የኅብረት ሥራ የሪፎርም ንቅናቄ ተጀምሮ የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወኑ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

የሪፎርም ሥራው አዋጅና ደንብ የማያስፈልጋቸው እስካሁን መሥራት ሲገባው ያልተሠሩ ተግባራትን መሥራት ቅድሚያ የተሰጠው መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር ጌታቸው፤ ሪፎርሙ ከዓመት በላይ ጊዜ ሊወስድ ይችላል ብለዋል፡፡

የማኅበራት ቁጥራቸው ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ ሀብታቸው፤ ጉልበታቸው ተበታትኗል፡፡ ከዚህ አንጻር አዋጁ የሚለው በአንድ ሥራ ክልል ውስጥ አንድ ተመሳሳይ የኅብረት ሥራ ማኅበር ካለ ሌላ ተመሳሳይ የኅብረት ሥራ ማኅበር መፈጠር የለበትም የሚለውን አዋጅ እንዲተገበር ማድረግ የሪፎርሙ አካል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ኮሚሽነሩ፤ የኅብረት ሥራ ማኅበራቱን ሊደግፍ እና ሊወክል የሚል ራሱን የቻለ ተቋም አለመኖሩ አንድ ችግር ነው፡፡ በሀገራችን ኅብረት ሥራ ማኅበራት፤ ዩኒየኖችና የፌዴሬሽን አደረጃጀቶች አሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህን ሰብሰብ አድርጎ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚወክል ተቋም እንዲኖራቸውና የራሳቸው ባንክ እንዲኖራቸው ማስቻል የሪፈርሙ አካል ነው ብለዋል፡፡

በዚህና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ከጌታቸው መለሰ (ዶ/ር) ጋር ያደረግነውን ሙሉ ቃለ ምልልስ በተጠየቅ ዓምዳችን ላይ ያገኙታል፡፡

# የጥናትና ምርምር ሥራዎች ትውልድ ግንባታ ላይ ሲያተኩሩ ይገባል

## - 14ኛው የኦሮሞ ጥናትና ምርምር ጉባኤ ተካሄዷል

**አማን ረሺድ**

አዳማ፡- የጥናትና ምርምር ሥራዎች ከነጠላ ትርክት ወጥተው በወል ትርክት የሚያምን ትውልድ ግንባታ ላይ ሊያተኩሩ እንደሚገባ በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የኦሮሚያ ክልል ማኅበራዊ ክላስተር አስተባባሪ አቶ አብዱልሐኪም ሙሉ ገለፁ። 14ኛው የኦሮሞ ጥናትና ምርምር ጉባኤ "እሴታችንን ለሀገር ግንባታ" በሚል መሪ ሀሳብ በአዳማ ከተማ ተካሂዷል።

አቶ አብዱልሐኪም በጉባኤው ላይ እንደገለፁት፤ የጥናትና ምርምር ሥራዎች የአሁኑ ትውልድ ካለፈው ታሪክ ተምሮ ለሀገር ግንባታ ሚናውን እንዲወጣ የሚረዱ መሆን አለባቸው።

በትውልድ ግንባታ ሂደት የጥናትና ምርምር ሥራዎች መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ ያሉት አቶ አብዱልሐኪም፤ በዚህ ረገድ የኦሮሞን ሕዝብ ባሕል፣ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና እሴት እንዲበልጽግ ድርሻቸውን የሚወጡ አካላት ምስጋና ይገባቸዋል ብለዋል።

የክልሉ መንግሥት የኦሮሞ ባሕል፣ ታሪክ፣ ቋንቋና ሌሎች እሴቶችን በአግባቡ ጠብቆ ለቀጣዩ ትውልድ እንዲያስተላልፍ በትኩረት እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

የዘንድሮ የኦሮሞ ጥናትና ምርምር ጉባኤ ኢትዮጵያ የዘመናት ጥያቄዋ የሆነውን የባሕር በር ባገኘችበት ወቅት መሆኑ ልዩ እንደሚያደርገው አቶ አብዱልሐኪም ጠቁመው፤ እያደገ ያለውን ኢኮኖሚያዊና ብሔራዊ ጥቅሞቿን ለማስጠበቅ ይረዳል፤ ይህን ውጤት ከትውልድ ግንባታ ጋር አስተሳስሮ ማስረጽ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የኦሮሚያ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ጀሚላ ሲንብሩ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ባለፉት ሥርዓቶች የኦሮሞ ሕዝብ የታሪክና ትርክት ስብራቶች የሚጠገኑት በስሜትና በቁጭት ሳይሆን በጥናትና ምርምር ሥራዎች ነው።

የተዛቡ ትርክቶች እንዲስተካከሉ፣ የሕዝቡ ባሕልና ወግ እንዲዳብር በጥናት የተደገፉ ሥራዎች ቀጣይነት እንዲኖረው ቢሮው አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።

እንደ ኃላፊዋ ገለጻ፤ ባለፉት ጊዜያት የጋራ ታሪኮችን ለሕዝብ ከማሳወቅ አንፃር አበረታች ሥራዎች መከናወናቸውን አመላክተው፤ ትውልድ ግንባታ ቀጣይነት ያለው ሥራ በመሆኑ የምርምርና ጥናት ሥራዎችን ከሀገር ግንባታ ጋር አያይዞ ማከናወን ይገባናል ሲሉ አስረድተዋል።

ኢንስቲትዩቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎችና የዘርፉ ባለድርሻ አካላት በሥነ ጽሑፍ፣ በታሪክ፣ በባሕልና በሌሎች ጉዳዮች ላይ በትብብር መስራት እንደሚገባቸውም ጠቁመዋል።

የኦሮሞ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ዲሪባ ተረፈ በበኩላቸው፤ የኢንስቲትዩቱ መመሥረት የረጅም ጊዜ የኦሮሞ ምሑራን ጥያቄ የመለሰ መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢንስቲትዩቱ በሁለት ዓመት ቆይታው የኦሮሞ ባሕል፣ ማንነት፣ ቋንቋ እሴት ላይ ጥናትና ምርምር እያከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

በተያዘው በጀት ዓመት በ60 ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ኢንስቲትዩቱ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን አመላክተው፤ በባሕል፣ እሴትና ቋንቋ ላይ አተኩረው የተፃፉ 72 መጻሕፍት ታትመው ሕዝብ ዘንድ መድረሳቸውን አስታውቀዋል።

ጥናትና ምርምሮቹ እንዲሁም የጽሑፍ ውጤቶቹ የወጣቶች ስብዕናን በማረቅ እንዲሁም በሀገር ግንባታው ላይ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያደርጉም ተናግረዋል።

በጉባኤው አባገዳዎችና ሀደ ሲንቄዎች፣ የማኅበራዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

# በከተማ አስተዳደሩ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኃላፊ ጣሰው ገብሬ (ዶ/ር)፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ እና የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ብርሃነመስቀል ጠና በጋራ መግለጫ ሰጥተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ ጣሰው ገብሬ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ታኅሣሥ 21 ቀን 2016 ዓ.ም ለከተማ አስተዳደሩ አመራር፣ ባለሙያ እና ሠራተኞች የተሰጠውን የቴክኒክና ባሕሪ ብቃት ፈተና የወሰዱት የከተማ አስተዳደሩ ሠራተኞች ቁጥር 15 ሺህ 151 ሲሆን ከዚሁ አጠቃላይ ቁጥር ለፈተና ከተቀመጡ 10 ሺህ 257 ፈፃሚዎች 5 ሺህ 95 ወይንም ከ50 በመቶ በላይ የሚሆኑት የማለፊያ ውጤት ማስመዝገብ ችለዋል።

በተመሳሳይ መልኩ ፈተናውን የወሰዱ ዳይሬክተር እና ቡድን መሪዎች ቁጥር 4 ሺህ 213 ሲሆን የፈተውን ማለፊያ ውጤት ያስመዘገቡት 34 በመቶ ወይንም 1 ሺህ 422 መሆናቸውን የገለጹት ዶክተር ጣሰው፤ ሠራተኞች ለማለፍ ከ50 በመቶ በላይ ማምጣት የሚጠበቅባቸው ሲሆን አመራሮች ደግሞ ለማለፍ ከ60 በመቶ በላይ ማምጣት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

በፈተናው ውጤት ላላመጡ አመራርና ሠራተኞች የአቅም ግንባታ ሥልጠና በመስጠትና ክህሎታቸውን የማብቃት ሥራ ይሠራል። በዚህም ደመወዛቸው ሳይነካ በሌሎች የሥራ መደቦች እንዲሠሩ ይደረጋል ብለዋል፤ የሠራተኞች ከሥራ የመሰናበት እድል ጠባብ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ለፈተና ከተቀመጠው አጠቃላይ ቁጥር 681 የሚሆነው በተለያየ የሥነ ምግባር ጥሰት ከፈተና ውጪ መሆናቸውን እና 441 የሚሆኑት ደግሞ በፈተና ስፍራ አለመገኘታቸውን ኃላፊው ጠቁመው፤ የፈተናው ዋና ዓላማ በከተማ አስተዳደሩ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ጥራት ለማረጋገጥ፣ በእውቀት የታገዘ ሲቪል ሰርቫንት ለመፍጠር፣ የተሻለ፣ ንቁ እና ብቁ አገልግሎት ሰጪ ለመፍጠር መሆኑን ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ በበኩላቸው፤ እያንዳንዱ ተፈታኝ የመፈተኛ መለያ ኮድ ተሰጥቶት ማንነቱ ሳይገለጥ እንዲፈተን ተደርጓል። ፈተናው ከዝግጅቱ አንስቶ እስከ ፈተናው እለት ድረስ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ሲሆን እርማቱም አራሚው የማንን እንደሚያርም እንኳን እንዲያውቅ እድል በማይሰጥ ሂደት ተከናውኗል ብለዋል።

በፈተናው ወቅት ተፈታኞች መልስ መስጫ ወረቀቶቹ ላይ ምንም አይነት ስም መፃፍ ያልተፈቀደ መሆኑና ስም ጽፈው ከተገኙ ፈተናው እንደማይታረምላቸው ቀድሞ እንደተነገራቸው እንዲሁም ኮድ መፃፍ ሲኖርባቸው ስማቸውን የፃፉ፤ ኮድ በትክክል ያልፃፉ፣ አጭር ኖት (አጤራራ) ይዘው የተገኙ እና በሌሎች ምክንያቶች ውጤት ያልተያዘላቸው 681 ተፈታኞች መኖራቸውን ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ ገልጸዋል።

የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ብርሃነመስቀል ጠና በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ከተማ አስተዳደሩ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በትብብር የቴክኒክና ባሕሪ ብቃት ፈተና እንዲያዘጋጁ የጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣታቸውን ገልጸዋል።

# "የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲን ለሀገራችን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ፣ የወጪ ንግዱን ለማሳለጥ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር የነፃ ንግድ ቀጣናዎች በመቀላቀል በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው ሰፊ ሥራ ተከናውኗል።

በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው በተሠሩ ሥራዎች ኢትዮጵያ በአፍሪካ ምርጥ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ከሚባሉ ሀገራት ውስጥ ተካታለች ያሉት አምባሳደር ምስጋኑ፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለምርቶቻችን አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት ረገድ በጎ ውጤት መገኘቱን አስረድተዋል።

በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ ኤምባሲዎችንና ቆንስላዎችን በመጠቀም እንዲሁም በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በኩል የኢንዱስትሪ፣ የማኑፋክቸሪንግና የቴክስታይል ዘርፍ ለአዳዲስ ምርቶች የገበያ ትስስር ለመፍጠር እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ኢንቨስትመንትን ከመሳብና አዳዲስ የገበያ መዳረሻችን ከመፍጠር አኳያ በዲፕሎማሲው በተለይ ከቻይና እና ከተለያዩ የእስያ ሀገራት እንዲሁም ከመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ጋር ትኩረት መደረጉን አምባሳደር ምስጋኑ አመላክተዋል።

ከቆዩ ወዳጅ ሀገራት ጋር ያለውን ትብብር የሚያጠናክሩ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ተቋርጠው የነበሩ ግንኙነቶችንም ዳግም በማደስ ታግደው የነበሩ የፋይናንስ ድጋፍና የሰብዓዊ ርዳታዎች እንዲጀምሩ መደረጉን አስታውሰዋል።

እንደ አምባሳደር ምስጋኑ ገለጻ፤ በተለያዩ ሀገራት የሚከፈቱ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች የሀገር ውስጥ ልማት እንዲሳለጥ በሚችልበት አግባብ እንዲቃኙ ማድረግ ይገባል።

በተጨማሪም ኢንቨስትመንት፣ የገበያ ዕድል፣ የቱሪዝም አቅምና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚገኙባቸው አካባቢዎችን ታሳቢ በማድረግ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲውን እንቅስቃሴ ማስፋፋት እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

# "ኢትዮጵያ ከሱማሊላንድ ጋር ያደረገችው የባሕር በር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ጥሩነህ ዜና አስታወቁ። ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መስክም ለአህጉሪቱ የተጫወተችው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

አምባሳደር ጥሩነህ፣ ከኢፕድ ጋር ባካሔዱት ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ ከሱማሊላንድ ጋር ያደረገችው የባሕር በር ስምምነት ጉዳይ በብልሃት ታስቦ በድፍረት የተከናወነ ነው። የተደረሰበትም ስምምነት ኢትዮጵያ የሚገባትን ከፍታ ለመያዝ የሚያስችላት ነው፡፡

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል እንዲህ አይነት ውሳኔ ለመወሰን ድፍረቱ እንዳልነበራት ጠቅሰው፤ ለዚህም ምክንያቱ እንደ ሀገር ጉዳት ይደርስብኛል ከሚል ስጋት የመነጨ ሊሆን እንደሚችል ተናግረዋል። ይሁንና ሁሌ በፍርሃት ውስጥ መሆን ዋጋ ስለሚያስከፍል ድፍረት አስፈላጊ ነው ሲሉ ተናግረው፤ ከሰሞኑ የተደረሰበት የባሕር በር ስምምነት በትክክለኛ ውሳኔ የታጀበ ድፍረት በመሆኑ መልካም ነው ብለዋል።

እንደ አምባሳደር ጥሩነህ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ የሚገባትን ከፍታ መያዝ ይኖርባታል። ለዚህም ደግሞ ወደከፍታዋ የሚያንደረድራትን ውሳኔዎች በብልሃትና በድፍረት መወሰን ይጠበቅባታል። ከዚህም አንዱ ከሰሞኑ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አማካይነት የተደረሰው የባሕር በሩ ስምምነት ማሳያ ነው። ውሳኔዎችን በድፍረት መወሰን ማለት ደግሞ ዝም ብሎ የመጣ አካሄድ ሳይሆን ግራ ቀኙ ነገሮችን በማየት የተደረሰበት ጉዳይ ነው። እዚህ ውሳኔ ላይ ሲደረስም ስለጉዳዩ ተጠንቶና ከብዙዎቹም ጋር ተመክሮ በመሆኑ ኢትዮጵያን "ባለህበት እርገጥ" ከሚባለው ፈሊጥ የሚያወጣትና ወደተፈለገው ከፍታ ለማሻገር የሚያስችላት ትልቅ እርምጃ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፤ "ትልቁን ስብራት አስቀምጠን ዝም ብለን መኖር የለብንም" ማለታቸውን ያስታወሱት አምባሳደር ጥሩነህ፣ ትልቁን ስብራት አላየሁም ብሎ መቀጠል የሚቻል አይደለም ብለዋል። ይህ በትልቅ ጥበብ እና አሳማኝ በሆነ ድፍረት የተካሄደው ስምምነት ጅማሬው እንዳማረ ሁሉ በጥቂት ጊዜያት በተግባር መለወጥ አለበት ሲሉ ተናግረዋል። ይህም ተግባር እየተከናወነ እንደሆነ እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል።

በእርግጥ የወደብ ጉዳይ አለ፤ በጂቡቲ በኩል እየወጣን ነው። ነገ ደግሞ በተመሳሳይ ከሌሎችም ጋር እንወጣለን። ነገር ግን የባሕር በር ሲባል ከወደብ የተለየ ነው። ባሕር በር ሲኖረን ተጭኖ ወደሀገራችን የሚገባ የትኛውም ሸቀጥ በሌሎች ቁጥጥር ስር የሚወድቅ አይሆንም። በተለይም ንብረታችን በሌሎቹ አካላት እንዳይጠለፍም ሆነ እንዳይጎዳ ያስችላል። ሸቀጣችንን እኛው ራሳችን አጅበን የምናመጣበት ሁኔታ ይፈጠርልናል። ከዚህ በተጨማሪ የባሕር ኃይላችንን በስፍራው መገንባት ስለሚያስችለን ሕልውናችንን ያረጋግጥልናል። ወደምንፈልገውም ከፍታ ለመዝለቅም ያስችለናል ብለዋል።

አምባሳደር ጥሩነህ፡- ኢትዮጵያ በአህጉራችን አፍሪካ በዲፕሎማሲው መስክ የተጫወተችው ሚና ከፍተኛ እንደሆነም አመልክተዋል። በተለይም ደግሞ የቀጣናውን ሠላም በማስጠበቅ ረገድ እና ሀገሮችን በማስተባበሩ በኩል ፊተኛውን መስመር የያዘች መሆኗን ገልጸዋል። በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ድምፃቸው እንዲሰማ በማድረግ ረገድም የተጫወተችው ሚና ላቅ ያለ እንደሆነ ተናግረዋል። ይህ ሚና ደግሞ እኛ ስለተናገርነው ሳይሆን በጉልህ የሚታይ ነው ብለዋል።

አምባሳደር ጥሩነህ እንዳሉት፤ አፍሪካ አሁን ያለችበት ደረጃ እንድትደርስም የተደረገበት ጊዜ አለ። ይኸውም በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግሥት እኤአ በ1960ዎቹ አካባቢ የአፍሪካን አንድነት በኢትዮጵያ አዲስ አበባ ውስጥ እንዲመሠረት ማድረግ ተችሏል። ይህም አፍሪካውያን ለመጀመሪያ ጊዜ የራሳቸው አቋም እንዲኖራቸው በማድረጉ በኩል የራሱ ሚና ያለው ነው፣ እንዲሁም በአንድ ድምፅ መናገር እንዲሞክሩም አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪም አፍሪካውያን ችግሮቻቸውን በራሳቸው ጥረት መፍታት እንዲችሉ ያደረገው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተቋቋመበት ጊዜ በመሆኑ ኢትዮጵያ የተጫወተችው ሚና እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው።

# ዘላቂና አስተማማኝ ወደብ - ለሁሉን አቀፍ ኢኮኖሚ ተጠቃሚነት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ወደብ ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ወሳኝ ሚና እንዳለው እሙን ነው:: በተለይ እንደኢትዮጵያ ላሉ ወደብ አልባ ሀገራት ደግሞ የህልውና ጉዳይ ነው:: ኢትዮጵያ ላለፉት 30 ዓመታት ወደብ አልባ መሆንዋ ለወጪ እና ለገቢ ንግድ የጅቡቲን ወደብ በመጠቀም ላይ ትገኛለች። ሀገሪቱ ለወደብ ኪራይ በየዓመቱ የምታወጣው ወጪ ከፍተኛ እንደሆነ ይነገራል::

ይህንን ችግር መፍታት ያስችል ዘንዳም መንግሥት በቅርቡ ከሱማሌ ላንድ ጋር ስምምነት አድርጓል:: ስምምነቱ ለሀገሪቷን የወደብ ጉዳይ ምላሽ የሚሰጥ እንደሆነ ታምኖበታል:: የወደብ መኖር ለኢኮኖሚው እድገት ያለውን ሚና አስመልክቶ ያነጋገርናቸው የፖሊሲ ባለሙያ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ፣ ወደብ የውጪና የገቢ ንግድ ከማሳለጥ ባሻገር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ይናገራሉ::

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ወደብ ላይ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ይገነባሉ:: ከቀረጥ እና ከግብር ነጻ አካባቢ ሆኖ ማምረቻ ቦታ ይሆናል:: ይህም እነ ቻይና እና አረብ ኤሜሪቶች ያደጉበት መንገድ ነው::

በተለይም ቀይባሕር ላይ በዓመት 160ሺ ቶን ዓሳ ማምረት እንደሚቻል የሚጠቅሱት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ይሁንና እስካሁን ድረስ በተወሰነ ደረጃ የሚጠቀሙበት ግብጽና ሳውዲ አረቢያ መሆናቸውን ያነሳሉ:: እነርሱ ደግሞ ኢኮኖሚያቸው ደህና የሚባሉ ሀገራት በመሆናቸውና የጎላ የኑሮ ችግር ስሌለባቸው ብዙም አይጠቀሙበትም ይላሉ:: ይሁንና ቀጣናው እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገራት ትልቅ ጥቅም እንደሚኖረው ያስረዳሉ::

በሌላ በኩል ባህር ውስጥ ከፍተኛ የማዕድን ሀብቶች መኖራቸውን የሚጠቅሱት ባለሙያው፤ ሱማሌ ላንድና ፑንትላንድ ባሉበት አካባቢ ከፍተኛ የነዳጅ ክምችት እንዳለ መረጋገጡንም ያነሳሉ:: በተጨማሪም ከፍተኛ መጠን ያለው የሰው ኃይል ለመቀጠር ያስችላል ይላሉ:: ወደቦች እየተስፋፉ ሄደው ብዙ ኩባንያዎች ቢሮዎቻቸውን እዚያ የሚከፍቱ መሆናቸውን አንስተው፤ ይህም ኢንዱስትሪዎች እየተስፋፉ ስለሚሄዱ ወደቦች አካባቢ በብዙ ሺ የሚቆጠር የሰው ኃይል መቅጠር እንደሚያስችል ይጠቁማሉ::

በራስ ወደብና በኪራይ ወደብ መካካል ስላለው ልዩነት አስመልክተው፤ ኢትዮጵያ ከጅቡቲ ለተከራየችው ወደብ በየወቅቱ ገንዘብ የምትከልፈበት ሲሆን፤ አሁንም ለወደብ ኪራይ በየዓመቱ በርካታ ዶላር ወጪ እንደምታደርግ ያስረዳሉ:: በሌላ በኩል ቻይና በራሺያና በሌሎች የአውሮፓ ሀገራት ያሉ ወደቦችን በሊዝ ወስዳ በማስተዳደር ለራሷ ጥቅም እንደምታውል ያነሳሉ:: ይህም ከኪራይ ዋጋ ሲነፃፀር ከፍተኛ እንዳልሆነ ነው የሚጠቁሙት::

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ በሊዝ ደረጃ የሚያዝ ወደብ ሲኖር ደግሞ ለተወሰነ ዓመት በሊዝ የሚቆይ ሆኖ በየዓመቱ ሊዝ ይከፈልበታል:: ያም ቢሆን ግን ከኪራዩ አንፃር ዝቅተኛ የሚባል ነው:: በተጨማሪም በሊዝ መሬቱ ተወስዶ የራስ ወደብ የመገንባት አሰራር ያለ ሲሆን ይህም የገነባው ሃገር ወደብ ይሆናል:: ኢትዮጵያም ወደብ ብትገነባ የምትከፍለው ሊዝ ለመሬቱ ብቻ ይሆናል::

በዚህ መንገድ ወደብ ሲገነባ ሁለቱንም ሃገር ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳሉ:: ‹‹ምክንያቱም የሚቀጠረው የሰው ኃይል ከዚያው ሀገር ነው የሚሆነው:: ከዚህ ባሻገር በገቢና በውጪ እቃ በተለያዩ መንገዶች ገበያ የሚያገኙበት መንገድ አለ፤ በአጠቃላይ በወደብ አካባቢ የሚያድገው የንግድ ልውውጥና የሚገነባው ኢንዱስትሪ ሁለቱንም የሚጠቅም ነው የሚሆነው›› ይላሉ::

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ አብዛኛው የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ በሱማሌላንድና በጅቡቲ በኩል እንደሚካሄድ ያመለከቱት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ የወደቡ መኖር ይህንን ችግር የማስቆም ከፍተኛ ጥቅም ይኖረዋል ባይ ናቸው:: ‹‹እንደ አገር የቀንድ ከብት፣ ቡና ፣ወርቅ የመሳሳሉ በኮንትሮባንድ መንገድ ስለሚካሄዱ ከፍተኛ የሆነ መዋለ ነዋይ እያሳጣን ነው›› ይላሉ::

ግሎባል ፋይናንሻል ኢንተግሬት የተሰኘ ድርጅት ያወጣ መረጃ ጠቅሰውም፤‹‹በኮንትሮባንድ ንግድ ኢትዮጵያ እስከ 3ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ብር ታጣለች›› ሲሉ ይጠቁማሉ:: እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ወደቡ በሱማሌላንድ ውስጥ የሕግ ማስከበር ሥራ የሚሰራ በመሆኑ ለኮንትሮባንድ ምቹ ሁኔታ እንዳማይኖር ያስረዳሉ::

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ትልቁ የንግድ መርከብ ድርጅት ያላት ሀገር መሆንዋን አስታውሰውም፤ እነዚህ መርከቦቻችን በከፍተኛ ገንዘብ ቢገዙም መርከቡ ማረፊያ ቦታ የሌላቸው በመሆኑ ለወደብ ኪራይ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ለማውጣት መገደዷን ያመለክታሉ:: በዚህም ረገድ የራስ ወደብ በሊዝ መገኘቱ ፋይዳው የጎላ እንደሆነ ያስገነዝባሉ::

በሌላ በኩልም በኤደን ባሕረ ሰላጤና በቀይ ባሕር አስቸጋሪ የጸጥታ ሁኔታ መኖሩን አስታውሰው ፤ይህንን ችግር መከላከል የሚያስችል የባሕር ኃይል መፍጠር ተገቢ መሆኑን ይናገራሉ:: ለዚህም ወደቡ ወሳኝ እንደሆነ ነው ባለሙያው የጠቀሱት::

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ አሁን ያለው የንግድ እንቅስቃሴ ተጨማሪ ወደብ መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ለጂቡቲ የሚከፈለው ከ1 ነጥብ5 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገንዘብ ሊቀንስልን ይችላል:: ይህ በአለም ውድ ኪራይ የሚከፈልበት የጅቡቲ ወደብ በየእለቱ ብዙ ትርምስ የሚያስተናግድ በመሆኑ የራስ ወደብ መኖሩ ሀገሪቱ ያለባትን እንግልት ያስቀርላታል:: የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ባደገ ቁጥርም ተጨማሪ ወደቦች ያስፈልጋሉ:: በተለይ የንግድ ልውውጡን አሁን ካለበት ደረጃ በላይ ለማዘመን የራስ ወደብ መገንባቱ የላቀ አስተዋፅኦ አለው:: በዚህ ረገድ የቻይና የመሳሰሉት ሃገራት ተሞክሮ የሚያሳየውም ይህንኑ ነው፤ ብለዋል::

‹‹በቅድሚያ ኢትዮጵያ ከሱማሌላንድ ጋር የምታደርገው የስምምነት በዲፕሎማሲ መንገድ መምራት ይጠበቅባታል›› ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ በመቀጠልም የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ መውሰድ እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ::

በሌላ በኩል በከፍተኛ ወጪ የተሰራው ጅቡቲ የባቡር መስመር ወደዚህ ማዞር ሊያስፈልግ የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ያነሳሉ:: ለዚህም ደግሞ ከሶማሌም ሆነ ከሌሎች ጎረቤት ሀገራት ጋር ሰላማዊ ግንኙነት መፍጠር ወሳኝ መሆኑን አንስተው፤ በተጨማሪም ሀገር ውስጥ ሰላምና መረጋገት እንዲሰፈን ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ነው ያስገነዘቡት::

ሌለኛው የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ተባባሪ ፕሮፌሰር ከተማ በቀለ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ዋናው የአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚለካው በጂዲፒ ነው:: እንደ ኢትዮጵያ ሲታይ ለጂዲፒው ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክተው የግብርና ዘርፍ ነው:: የግብርናው ዘርፍ የሚውሉ አብዛኞቹ ግብዓቶች ከውጭ የሚመጣ በመሆኑ፤ እንዲሁም የግብርና ምርቶችም ወደተለያዩ ሃገራት የሚላክ እንደመሆኑ የራስ ወደብ መኖሩን ይህንን የንግድ ልውውጥ ለማሳለጥ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው:: በተለይም በኪራይ ግብዓቶች የሚገቡ ከሆነ ዋጋቸው የሚጨምር በመሆኑ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ሚና ይኖረዋል::

‹‹አሁን ላይ ለጂቡቲ ወደብ ኪራይ የሚወጣው ወጪ ማዳበሪያ ላይ ዋጋ እንዲጨምር በማድረግ አርሶ አደሩ ጋር ሲደርስ ድረስ ዋጋው የጨመረ እንዲሆን ያደርገዋል›› ይላሉ:: ይህ ደግሞ አርሶ አደሩ ምርት ላይ ተደምሮ ሲቀርብ የዋጋ ንረት እንዲመጣ እንደሚያደርግ ይጠቁማሉ::

በተጨማሪም መዘግየት እንደሚፈጥር የሚያነሱት ተባባሪ ፕሮፌሰሩ፤ ‹‹የራሳችንን ወደቡ ቢኖር የሚፈለገው የግብርና ምርት ቀድሞ ማምጣት የሚቻልበት ሁኔታ መፍጠር ይቻል ነበር:: አሁን ላይ የወደቡ ላይ የሚከማችበትን ወጪ ላለመክፈል በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማምጣት የሚቻልበት ስትራቴጂ ነው ተግባራዊ እየተደረገ ያለው:: ይህንን ስንል ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች መጉላላቶች ስለሚፈጠሩ ለምርት ጊዜ ሳይደርስ ይቀርና መዘግየት እንዲከሰት ያደርጋል›› ሲሉም ያስረዳሉ::

ከዚህም ባሻገር ወደ ውጭ የሚላከው ምርት ዋጋ የወደቡ ኪራይ ተጨምሮ ስለሚሰላ በተቀባይ ሀገራት ፍላጎት እንዲቀንስና ሌላ በተሻለ ዋጋ የሚያቀርቡ ሀገራት ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ምክንያት ይሆናል የሚል እምነት አላቸው:: በተመሳሳይ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ምርት ላይ ዋጋ እንዲጨምር የሚያደርግ መሆኑን አንስተው፤ በመሆኑም የወደቡ መኖርን በዚህ ምክንያት የሚፈጠረውን የዋጋ ንረት የሚያስተካክል እንደሆነም ነው ያስረዱት::

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ ኢትዮጵያ ከሱማሌላንድ ጋር ያደረገችው የወደብ ስምምነት የውጭና የገቢ ንግዱን ከማሳለጥ ባሻገር ዘርፈ ብዙ የኢኮኖሚያዊ ጥቅም አለው:: የኢትዮጵያ መንግሥት ይህንን ስምምነት ሲያደርግ የሁለቱንም ሀገራት በማይጎዱ መልኩ የንግድ ሂደቱን ለማሳለጥ ያግዛል:: የዚህ ወደብ መኖር የጅብቲን ወደብ እንደሌላ አማራጭ ለመጠቀም ያስችላል:: ሁለቱንም ወደቦች በመያዝ አመቺ የሆነው አማራጭ በመጠቀም የንግድ ሂደቱን ለማቀላጠፍ ይረዳል::

‹‹መንግሥት በወደቡ ዙሪያ ከሱማሌላንድ ጋር ያደረገው ስምምነት ተከትሎ አሁን ላይ እየተነሱ ያሉ ጉዳዮች እልባት ሊያገኙ ይገባል›› የሚሉት ተባባሪ ፕሮፌሰሩ፤ የቀይባሕር ጉዳይ የቀጠናው ሀገራትን ብቻ የሚመለከት ጉዳይ ሳይሆን ትልልቅ ሀገራት አጀንዳ እንደሆነ ያመላክታሉ:: ምክንያቱም ሲያስረዱ ‹‹የዓለማችን 12 በመቶ ሸቀጥ በቀይ ባሕር ስለሚያልፍ ነው፤ ስለዚህ መንግሥት ከሌሎች ሀገራት ጋር በምን መልኩ መሄድ እንደምችል በሰከነ መንፈስ በመወያየት የሚያስችል የዲፕሎማሲ ሥራዎች መስራት ያዋጣል›› ይላሉ::

ኢትዮጵያ ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን ከሰራች የሱማሌላንድ ወደብ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ብዙ አማራጮችን በማስፋት መጠቀም እንደምትችል አንስተው፤ አማራጮችን ማስፋቷ ደግሞ ዘላቂና አስተማማን የወደብ አማራጭን ከማግኘት ጀምሮ ለኢኮኖሚ እድገቷ የላቀ ጠቀሜታ እንዳለው ነው ተባባሪ ፕሮፌሰሩ ያስገነዘቡት::

**ኢትዮጵያ ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን ከሰራች የሱማሌላንድ ወደብ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ብዙ አማራጮችን ማስፋት ትችላለች። አማራጮችን ማስፋቷ ደግሞ ዘላቂና አስተማማኝ ወደብን ከማግኘት ጀምሮ ለኢኮኖሚ እድገቷ የላቀ ጠቀሜታ አለው**

# ተንቀሳቃሽ ጭፈራ ቤቶች

**እዮሩስ ተስፋዬ**

የገባሁበት ታክሲ ከቦሌ ወደ ፒያሳ የሚያደርሰውን ነበር:: ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሊሆን የቀሩት ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ናቸው:: ወደ ታክሲው ስገባ ሠላም አልተሰማኝም:: በጣም ደመቅመቅ ያሉ መብራቶች (ዲምላይት) የታክሲውን ጥጋጥግ እንዲሁም መሐል ላይ ተለጥፈው ለዓይን ምቾት አይሰጡም:: ታክሲው ለትራንስፖርት አገልግሎት ብቻ የተዘጋጀ መሆኑም ያጠራጥራል:: በጣም በከፍተኛ ድምፅ የተከፈተ ስልተ ምቱ ‹አፍሮ ቢት› ይሉት አይነት ሙዚቃ ታክሲውን ድብልቅልቅ አድርጎታል::

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ስልክ ማውራት አይሞከርም:: አጠገብ ካለው ሰው ጋር መነጋገር የሚቻለው በምልክት ብቻ ነው:: አልያ ደግሞ ወደ ጆሮ ጠጋ ብሎ መናገር ግድ ይላል:: ብቻ ምን አለፋችሁ ታክሲው አስተናጋጅ እና መጠጦች የሌሉበት ጭፈራ ቤት መስሏል:: እኔ በግሌ እንዲህ ያሉትን ታክሲዎች እና መሰል የትራንስፖርተ አገልግሎት ሰጪዎችን ‹‹ተንቀሳቃሽ ጭፈራ ቤቶች›› ብያቸዋለሁ::

ደግሞ እኮ ሙዚቃው ማቆሚያ የለውም:: የሹፌሩ አነዳድም ልክ እንደ ሙዚቃው የፈጠነ ነበር:: በመሐል አነዳዱ ሳያምረን ሲቀር ‹‹ኸረ ቀስ በል::›› ብንለው ሰሚ አናገኝም:: የምንለውን ለመስማት የግድ የሙዚቃው ድምፅ መቀነስ አለበት:: ሙዚቃው ከፍ ብሎ በመደመጡ፤ ንግግሮች ሁሉ አየር ላይ ይቀራሉ:: በጉዟችን መሐል አንድ ስልክ ለማውራት የሞከረች ሴት መደማመጥ አቃታት:: ‹‹እባክህ ሾፌር ድምፁን ትንሽ ቀነስ ብታደርገው?›› ብላ በትሕትና ብትጠይቅ፤ ወይ ፍንክች:: አጠገቤ ስለነበረች የሰማኋት እኔ ብቻ ሳልሆን አልቀርም:: ያላት አማራጭ ረዳቱን መጎተት ነበር:: እርሱም ሂሳቡን ከሰበሰበ በኋላ የሚመለከተው ወደ ፊት ብቻ ነበር:: እንደ ምንም ፊቱን ወደ ኋላ አዞሮ ‹‹እእእ ... ምን ፈለግሽ?›› አላት እርሷም ‹‹ወይ ቀንሰው፤ ወይ ዝጋው፡፡ መደማመጥ አልቻልኩም›› አለችው:: በመሐል ሹፌሩ ጭቅጭቅ እንደተፈጠረ ገብቶት የሙዚቃውን ድምፅ በመቀነስ ‹‹ከፈለክሽ ውረጂ›› የሚል መልስ ሰጣት:: በዚህ መሐል ብዙ ጭቅጭቅና ንትርክ ተፈጥሮ እንደ ምንም ‹‹በሠላም›› ካሰብንበት ደረስን::

> በትራንስፖርት መጓጓዣዎች ውስጥ የሚደረጉ አንዳንድ ክንውኖች አንዳች የሚያመላክቱት የግብረ ገብ ጉድለት መኖሩን በግሌ አምናለሁ

የተፈጠረውን ንትርክ እያሰብኩ ለራሴ ‹‹እንኳንም አጭር መንገድ ሆነ›› አልኩ:: እንዲህ አይነቱ ችግር በብዛት በትራንስፖርት ውስጥ ያጋጥማል:: ሙዚቃዎች እና መንፈሳዊ መዝሙሮች ከመጠን በላይ ድምፅ ተከፍተው ‹‹ቀንሱ›› ከተባሉ ነገሩን ከሌላ ነገር ጋር ያይዙታል:: የሕዝብ ትራንስፖርት ሕዝቡን ለማገልገል የተዘጋጁ ናቸው:: ነገር ግን አንዳንዶቹ ከዓላማቸው ያፈነገጡ ሆነው ነው የሚገኙት::

የትራንስፖርት መጓጓዣዎች ጥቅማቸው ብዙ ነው:: አንዳንዶች ከራሳቸው ጋር ለመነጋገር ይጠቀሙበታል:: ረዘም ያለ ቦታ የሚሄዱት ደግሞ የተለያዩ መጽሐፎችን በማንበብ ይጠቀሙበታል:: በተጨማሪም የብዙ ሰዎች መተዋወቂያ ስፍራ ሲሆኑ፤ ከተነፋፈቁት ወዳጅ፣ ጓደኛ፣ ዘመድ እና ቤተሰብ ጋር ሳይቀጣጠሩ በአጋጣሚ የሚገናኙበት ዕድል ሰፊ ነው ማለት ይቻላል::

እንደ እድል ሆኖ እኔ የተሳፈርኩበት ታክሲ በስፒከር ብቻ የታጀበ ነበር:: አንዳንዶቹ ደግሞ በተንቀሳቃሽ ምስል ጭምር የታገዙ ናቸው:: የሕዝብ ትራንስፖርትን በእድሜ ከፍ ካሉ አረጋውያን ጀምሮ ሕፃናት እና ወጣቶች ይገለገሉበታል:: አንዳንድ ባለታክሲዎች የሚከፍቱት የሙዚቃ ቪዲዮዎች ፍጹም ከባሕላችን እና ከወጋችን ያፈነገጡ ናቸው:: እርቃናቸውን የሚደንሱ ሴቶችን እና አልባሌ ድርጊቶቻቸውን ላለመመልከት ገሚሱ በሀፍረት ሲሸማቀቅ፤ ገሚሱ ደግሞ ተገቢ እንዳልሆነ ለማስተማር ለመምከር ገና ከጅማሬው ስድቡን ተከናንቦ ይወርዳታል::

አንዳንድ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ለተሳፋሪዎቻቸው አስቂኝ፣ አስተማሪ እና መላ (ዘዴን) የሚያስተምሩ ቪዲዮዎችን በመክፈት ‹‹ይህም አለ ለካ?›› የሚያስብሉ መልዕክቶችን በማሳየት ተሳፋሪዎቻቸው ከቦታ ቦታ ከመጓጓዝ ባለፈ ለማስተማር የሚያደርጉትን ጥረት አመስግኖ ማለፍ ተገቢ ነው::

አሁን አሁን ታክሲ ላይ አስተያየት መስጠት ፍጹም የማይታሰብበት ሜዳ ከሆነ የዕለት ተዕለት ትዝብታችን ሆኗል:: ሰዎች ‹‹ለምን እሰደባለሁ›› ብለው መብታቸውን አሳልፈው የሚሰጡበት ቦታም ሆኗል:: የትራፊክ ፖሊሶቻችን ይሁኑ ሌሎች የሕግ ተቆጣጣሪ አካላት የሚመለከቱት ትርፍ የመጫናቸው እና ሌሎችን ሕግ ስለመተላለፋቸው ብቻ ነው::

በታክሲም ሆነ በሌሎች መጓጓዣዎች ‹‹እየተረበሸኩ ነው›› ብሎ ተሳፋሪው አይከስ ነገር ድምፅ መጨመሪያውም ሆነ መቀነሻው ያለው በሾፌሩ እጅ ነው:: ምን ይታወቃል? ዝም ብሎ ከመሳፈር ውጭ እንዲህ አይነቱን ሃሳብ ማንሳት በራሱ ቅንጦት (ቀበጥ) ያስብል ይሆናል:: ‹‹ታክሲውን እናግኘው እንጂ ለምን ከዛ በላይ አይናገሩንም›› የሚል ሃሳብ ከአንዳንድ ሠዎች እንደሚሰነዘር ይታወቃል::

በእርግጥ ስለ ሾፌሮች እና ረዳቶች ይህን አልን እንጂ በተሳፋሪዎችም የሚታየው ችግር ብዙ ነው:: ምን እንደሆነ ባይገባኝም በትሕትና ከማናገር ይልቅ ለጸብ የሚጋብዝ ንግግር ይስተዋላል:: ሁሉንም አጥፊ እና ተሳዳቢ አድርጎ በመቁጠር አገልግሎት የሚሰጡትን ሰዎች ሥነ ምግባር በጎደለው መልኩ ሲያናግሩ እና ሲያደናግሩ ይታያል:: አንዳንዶችም በስልካቸው የተለያዩ ሙዚቃዎችም በሉት ቪዲዮ በመክፈት እና በስልክ ጥሪያቸው ተሳፋሪዎችን በመረበሽ መውረጃ ቦታን ያስናፍቃሉ::

ይህን፣ በትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለውን ችግር አነሳን እንጂ መረጃ አሰጣጥ ላይ ብዙ ክፍተቶች ይታዩብናል:: አንድ ጥያቄ ተጠይቆ ምላሽ መስጠትን እንደ ትልቅ ነገር ማየት በአንዳንድ ቦታዎች የተለመደ ነው:: በትሕትና ከማናገር ይልቅ በቁጣ ማስረዳት፤ ከመጨቃጨቅ እስከ መሰዳደብ ደረጃም ይደረሳል:: ሥራ እየሠሩ ሥራ ካለመሥራት የማይተናነስ፣ የመሰልቸት ስሜት የሚስተዋልባቸው አገልጋዮች ጥቂቶች አይደሉም::

ትንሽ ጩኸት የሚረብሻቸው ሰዎች ምን ዓይነት ችግር ሊገጥማቸው እንደሚችል መገመት ቀላል ነው:: አንዳንዶቹ የሚከፍቱት ሙዚቃ ተሳፍሮ ከሚሄደው ውጭ ለመንገደኛ እስከ መሰማት የደረሰ ነው:: ይህንን የሰማ መንገደኛም በሙዚቃ ለሚረበሸው ተሳፋሪ ከማዘን ውጭ ሌላ ምን ማድረግ ይቻለዋል?

በትራንስፖርት መጓጓዣዎች ውስጥ የሚደረጉ አንዳንድ ክንውኖች አንዳች የሚያመላክቱት የግብረ ገብ ጉድለት መኖሩን በግሌ አምናለሁ:: በዚህም ለሰው ግድ ያለመስጠት፣ ራስ ወዳድ መሆን፣ ሥራን እንደ ሥራ አክብሮ አለማየት፣ የሥነ ሥርዓት እጦት፣ እንዴት ማገልገል እና መገልገል እንደሚገባን ጠንቅቆ አለማውቅን እና ሌሎችንም ታዝቤያለሁ:: ለዚህም ይሆናል አንዳንዶቹ የሰውን መረበሽ ከምንም የማይቆጥሩት:: ብቻ ይህ ሊሆን የሚችለው በራስ ስሜት ብቻ ከመነዳት፣ ሥራን እንዴት መሥራት እንደሚገባ ጠንቅቆ ካለማወቅ የመጣ የግንዛቤ ችግር ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ::

ለማንኛውም የድምፅ ብክለት የሚከሰተው ከጭፈራ ቤቶች ብቻ ከሚወጡ ድምጾች ብቻ አይደለም፤ በተመሳሳይ ከተንቀሳቃሽ ጭፈራ ቤቶቻችን ጭምር እንጂ::

# ዓለም አቀፍ



## ለቻይና ወታደራዊ ምሥጢር የሰጠው የአሜሪካ ባሕር ኃይል ኃላፊ በእስራት ተቀጣ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ጥብቅ ወታደራዊ መረጃ ለቻይና እንደሰጠ ያመነው የአሜሪካ ባሕር ኃይል ባለሥልጣን የሁለት ዓመታት እስር ተፈረደበት። በካሊፎርንያ የባሕር ኃይል ይሠራ የነበረው ዌንሄንግ ዣዎ የተባለው የ26 ዓመት ግለሰብ ባለፈው ጥቅምት ለቻይና ስለላ ተቋም መረጃ እንደሰጠና ጉቦም እንደተቀበለ አምኗል።

አሜሪካ በኢንዶ-ፓስፊክ ቀጠና ያላትን የባሕር ላይ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ምሥጢር ነው አሳልፎ የሰጠው። ስለ ወታደራዊ እንቅስቃሴ፣ የኦፕሬሽን ትዕዛዞችና እአአ ከ2021 እስከ 2023 ያለውን የመሠረተ ልማት መዋቅር ነው መረጃ እንዳስተላለፈ የተገለጸው።

አሜሪካ በቀጠናው ካላት ወታደራዊ እንቅስቃሴ ባሻገር የኤሌክትሪክ ዲያግራሞችና ረቂቆችም ሰጥቷል ተብሏል። አሜሪካ በጃፓኗ ደሴት ኦኪናዋ ባላት ወታደራዊ መቀመጫ ስላለው መቆጣጠሪያ መሣሪያ ረቂቅ መረጃ አሳልፎ መስጠቱም ተጠቅሷል።

አሜሪካ በጃፓን ደሴት ያላት ወታደራዊ መቀመጫ በእስያ ለምታደርገው እንቅስቃሴ ቁልፍ ነው። ቀጠናውን የደኅንነት ጉዳዮች ዋነኛ መዳረሻ ያደረገችው አሜሪካ፣ የቻይናን ወታደራዊ እንቅስቃሴ ለመገዳደር ባለፉት ዓመታት የተለያዩ የጥምረት ሥራዎች በአካባቢው እያከናወነች ነው።

ከአጋር አገሮች ጋር በመሆን በቀጠናው ወታደራዊ ልምምድ አጠናክራለች። መረጃውን አሳልፎ የሰጠው ግለሰብ ሁኔሜ በተባለ አካባቢ በሚገኝ ወታደራዊ መቀመጫ ነበር የሚሠራው።

የአሜሪካ የፍትሕ ሚኒስቴር እንዳለው በጥብቅ ወታደራዊ ስፍራዎች በመግባት መረጃ ሰብስቧል። “ውስብስብ የግንኙነት መስመር በመጠቀም መረጃውን አስተላልፏል” ተብሏል።

መረጃዎቹን ከላከ በኋላ በማጥፋት ከቻይና የስለላ ተቋም ጋር ያለውን ግንኙነት መደበቁም ተገልጿል። እ.አ.አ. ከነሐሴ 2021 እስከ ግንቦት 2023 ባሉት ጊዜያት ቢያንስ 14 ጊዜ ወደ 14 ሺህ 866 ዶላር ገደማ ተከፍሎታል።

ግለሰቡ የተወለደው ቻይና ሲሆን በዜግነት አሜሪካዊ ነው። እ.አ.አ. በ2009 ወደ አሜሪካ ገብቷል።

የአሜሪካ የፍትሕ ሚኒስትር ምክትል ዐቃቤ ሕግ ጀነራል ማቲው ኦንሰል እንዳሉት የቻይና የስለላ ተቋም በአሜሪካ ወታደራዊ መዋቅር ውስጥ ጥብቅ መረጃ የማግኘት ይሁንታ ያገኙ ባልደረቦችን ዒላማ ያደርጋል። በገንዘብ ያታልሏቸውና ጥብቅ የመንግሥት መረጃ ይወስዳሉ ብለዋል።

አምና ጂንቻኦ ዌይ የተባለ የ22 ዓመት ግለሰብም ለቻይና ብሔራዊ መረጃ በማቀበል መከሰሱ ይታወሳል። ሁለቱን ግለሰቦች ለስለላ የመለመለው የቻይና ስለላ ክንፍ ተመሳሳይ ስለመሆኑ ግልጽ መረጃ የለም።

## የካንሰር ህዋስን 99 በመቶ መግደል የሚያስችል ግኝት ማግኘታቸውን ተመራማሪዎች ገለጹ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የካንሰር ህዋስን 99 በመቶ መግደል የሚያስችል ግኝት ማግኘታቸውን ተመራማሪዎች ገለጹ፡፡

በዓለማችን በሕመም ምክንያት ከሚከሰቱ 10 የሰው ልጅ ሞቶች ውስጥ ስድስቱ በካንሰር እንደሚሞቱ የዓለም ጤና ድርጅት ያስረዳል፡፡

ይህ የጤና እክል ሳይባባስ ከታወቀ በሚደረጉ ተከታታይ ሕክምናዎች መዳን ቢቻልም ብዙዎቹ ግን የካንሰር መጠኑ ከተባባሰ በኋላ ወደ ሕክምና ተቋማት እየመጡ መሆኑ በካንሰር የሚሞቱ ሰዎችን ቁጥር እንዲጨምር አድርጎታል፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ የጤና ተመራማሪዎች ለካንሰር ፈዋሽ መድኃኒት ለመሥራት በየጊዜው ለውጦች ቢኖሩም እስካሁን ግን በፈዋሽነቱ የተረጋገጠ መድኃኒት አልተገኘም፡፡


የአሜሪካ ተመራማሪዎች የካንሰር ህዋስን 99 በመቶ መግደል መቻሉን አረጋግጠናል ብለዋል፡፡

ተመራማሪዎቹ በቤተ ሙከራ ውስጥ አደረግነው ባሉት ጥረት ካንሰር ህዋስ ይገኝበታል በተባለው ስፍራ ላይ ኃይል በኢንፍራሬድ በማስገባትና በአካባቢው ማዕበል እንዲከሰት በማድረግ የካንሰር ህዋሱን መግደል ተችሏል ብለዋል፡፡

በአሜሪካ ሪስ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪ የሆኑት ሲሰሮን አይላ አሮዝኮ ለዩሮ ኒውስ እንዳሉት የካንሰር ህዋስን መግደል እንደሚቻል አረጋግጠናል ብለዋል፡፡

ተመራማሪዋ አክለውም ከእንግዲህ ዋናው ጉዳይ የሚሆነው ይህን በማዕበል የካንሰር ህዋስን የመግደል ግኝት ለሰው ልጆች ሕክምና በሚሆን መልኩ ወደ መድኃኒትነት የመቀየሩ ሥራ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

እንደተመራማሪዋ ገለጻ የካንሰር መድኃኒት የማዘጋጀት ሥራው ግኝቱ ሊያደርስ የሚችለው የጎንዮሽ ጉዳት ከተጠና በኋላ በመሆኑ ከ10 እስከ 15 ዓመት ሊፈጅ ይችላል፡፡



# ነፃ ሃሳብ

# በጎ ተስፋ ይዞ የመጣው ስምምነት

**ታሪኩ ዘለቀ**

ሪቻርድ ፓንክረስት ጥንታዊ ነጋዴዎች በጉዞ ማስታወሻቸው ያሰፈሯቸውን ጥንታዊ ፅሁፎች በመሰብሰብ ‹‹ኢትዮጵያ ከቀይ ባህርና ከህንድ ውቅያኖስ ማዶ›› በሚል ርዕስ ፅሁፍ አስነብበው ነበር:: በዚህ ፅሁፋቸው ከአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ መካከለኛው ዘመን ድረስ ህንድና ኢትዮጵያ በቀይ ባህርና በህንድ ውቅያኖስ በኩል ጠንካራ የንግድ ልውውጥ ያደርጉ እንደነበር አስፍረዋል::

በኤደን ባህረ ሰላጤ በኩልም ኢትዮጵያ ጠንካራ የንግድ ልውውጥ ታደርግ እንደነበር ፤አንድሬ ያኩሳል የተባለ ጥንታዊ የቬነስ ነጋዴ ያሰፈረውን ማስታወሻም አጣቅሰው ጽፈዋል ፤ ጸሀፊው በየመን ጠረፍ ላይ የምትገኘውን የኤደን ወደብ ዋንኛው የአረቢያና የኢትዮጵያ ወደብ ሲል በጽሁፉ ማስፈሩንም እንዲሁ ::

ሀገረ ኢትዮጵያና የባህር በር ታሪክ ሲነሳ የኋልዮሽ ሺህ ዘመናትን ሊሻገር ይችላል:: በየመንግስታቱ የይገባኛል መብት ሲነሳበት ሙግትና ድርድር አበቅ የለሽ እልህ አስጨራሽ ግንኙነት ሲደረግበት :: ከደርግ መንግስት በኋላ ግን ሀገሪቱ ያላት የባህር በር መብት ተቋርጦ ከርሟል:: የዜጎች ቁጭትም እያደር ሲባባስ ነው የመጣው::

ባለፉት ሶስት አስርት አመታትም የጅቡቲን ወደብ በመጠቀሟ ለወጪና ገቢ ንግድ በየአመቱ በርካታ ገንዘቦችን ለጅቡቲ ፈሰስ አድርጋለች:: አሁን ያለውን አመታዊ ክፍያ እንኳ ብንመለከት ከ164 ቢሊዮን ብር በላይ ደርሷል:: ይህ ደግሞ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ምን ያህል ተፅእኖ እያሳደረ መሆኑን መረዳት ይቻላል::

የባህር በር አልባነት የወለደው የዜጎች ቁጭት ከዚህ በፊት ታላቅ ከነበርን አሁንም ታላቅ መሆን እንችላለን የሚል መንፈስን ያዘለ ነው:: ኢትዮጵያ ከሱዳን አንስቶ እስከ ታንዛኒያ ድረስ ያሉትን ወደቦች መጠቀም የምትችልባቸው በርካታ አማራጮች አሏት:: ከከበቧት ሀገራት ጋር ተወያይታ፣ተነጋግራ ሰጥቶ በመቀበል መርህ የባህር በር ታገኝ ዘንድ ቀጠናዊ ውይይት እንደሚያሻ ግልፅ አድርጋለች::

የባህር በር ጥያቄዋን በድርድር በሰጥቶ መቀበል እና በሰላማዊ አማራጭ የዲፕሎማሲ ጥረቷን አጠናክራ እንደምትቀጥል አስታውቃለች:: የኢትዮጵያ የባህር በር ተጠቃሚ መሆን ከራስ ጥቅም አልፎ ለቀጠናው ሀገራት ዘላቂ ሰላምና የጋራ ተጠቃሚነት የላቀ አስተዋፅኦ አለው፡

ሀገራት ባላቸው የቆዳ ስፋት መጠን ከተለያዩ ሀገራት ጋር ይዋሰናሉ:: በዚህም ምክንያት በባህር በር አጠቃቀም ረገድ የተለያዩ ስምምነቶችን በመፈፀም የጋራ ተጠቃሚነት ላይ ያተኮረ ስራንም ይተገብራሉ:: አንዳንድ ሀገራት ደግሞ ልዩነታቸውን በውይይት መፍታት ባለመቻላቸው ምክንያት ለጦርነት ሲዳረጉ ይስተዋላል:: እ.ኤ.አ በ1879 ቦሊቪያ እና ፔሩ በጋራ ሆነው ከቺሊ ጋር ያደረጉት ‹‹ዋር ኦፍ ፓስፊክ›› የተሰኘ ስያሜ የተሰጠው ጦርነት ተጠቃሽ ነው::

ክስተቱ ከግጭት ይልቅ ስምምነት አማራጭ የሌለው ተመራጭ መፍትሄ መሆኑን ታይቶበታል::በአለማችን ከሚገኙ ሀገራት መካከል 169ኙ አለም አቀፍ የባህር ስምምነትን ተፈራርመዋል:: ሀገራችን ኢትዮጵያም የዚሁ አካል ናት:: ኢትዮጵያ ከሰላሳ አመታት በኋላ ያጣችውን የባህር በር ተጠቃሚነት ጥያቄዋ አሁን ላይ ዋንኛ አጀንዳ አድርጋ ይዘዋለች:: ጥያቄዋም በጎ ምላሽ ማግኘት ጀምሯል::

የባህር በር ለአንድ ሀገር ምጣኔ ሀብታዊ እድገትና ስትራቴጂያዊ ጥቅሙ የጎላ መሆኑ ይታወቃል:: በአለማችን የሚገኙና የባህር በር ባለቤት የሆኑ ሀገራት በየአመቱ ከዘርፉ በቢሊዮን የሚቆጠር ሀብትን ከኪራይ ገቢ ያገኛሉ ። በተቃራኒው የባህር በር ያላቸው ሀገራት ወደ ሀገራቸው ለሚያስገቡትና ለሚያስወጡት ሸቀጦቻቸው ምንም አይነት ክፍያ ባለመክፈላቸው በቢሊዮን የሚቆጠር ወጪ ያድናሉ::

አሁን ላይ ኢትዮጵያ በበርካታ መሰረተ ልማቶቿ በመገንባት ፤ ለከአካባቢው ሀገራት ጋር ሁለንተናዊ ትብብርና የልማት ትስስር እየፈጠረች ነው:: የባህር በር ጥያቄዋም የዚህ አብሮ የመልማት ጉዳይአካል ነው:: የሀገሪቷ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲም ቢሆን መልካም ጉርብትናን፣ የጋራ ተጠቃሚነትን፣ አጋርነትንና ትብብርን መሰረት ያደረገ ነው::

በአለም አቀፉ የሀገራት ግንኙነት ውስጥ ትልቅ ስፍራ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል ዋናው የዲፕሎማሲ ግንኙነት ነው:: ኢኮኖሚያዊ ፣ፖለቲካዊ እና ወታደራዊ የሚባሉት ዘርፎች እንዳሉ ሆነው ዲፕሎማሲው ግን ሁሉንም የማስተሳሰርና የማጣመር ሀይል አለው::

ወታደራዊ ጡንቻ ከዲፕሎማሲያዊ ውጤት ውጪ ሌሎችን ከማስፈራራትና በሌሎች ከመጠላት የዘለለ ውጤት የለውም:: የኢኮኖሚ የበላይነትም ከዲፕሎማሲ ውጪ የራሱን ምኞት ከመስጠት ተሻግሮ በሌሎች ዘንድ ከበሬታንና ተፈላጊነትን አያመጣም:: ዲፕሎማሲ ግን እነዚህን ወደራሱ በፍቅር የመሳብ ሀይል ይኖረዋል::

ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መስክ ያላት ከበሬታ ለብዙ ድሎች እያበቃት ነው:: ለጊዜው ሌሎቹን አቆይተን ባሳለፍነው ሳምንት ኢትዮጵያ ከሱማሌ ላንድ ጋር ያደረገችው የወደብ ስምምነት ትልቅ የዲፕሎማሲ ትግል ውጤት ነው:: ዲፕሎማሲ ዝምብሎ ከሰማይ የሚወርድ ሳይሆን የብዙ ድሎች ውጤት ነው::

ሀገራት ኢትዮጵያን አጋራቸው አድርገው ሲቀበሏ ስለምታስፈልጋቸው እና ስለምትጠቅማቸው ነው:: የድሮ ገናናነቷና ታሪኳ እንዳለ ሆኖ በተለይ የአሁኑ አያያዟን አስቀጥላ ወደፊት የምትደርስበት ደረጃን በመተንበይ ሀገራት እንደአንድ አጋር እንዲመለከቷት አድርጓቸዋል::

በተለይም ከሱማሌ ላንድ ጋር ያደረገችው የወደብ ስምምነት ትልቅ ጥቅም ይዞላት መጥቷል:: በየአመቱም 25 በመቶ በላይ ገቢዋን የምትገብርለት የወደብ ጉዳይ በዚሁ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ መፍትሄ ማግኘት ጀምሯል ማለት ነው:: በሌላት የውጭ ምንዛሬ በየአመቱ 1 ነጥብ 5 ሚሊየን ዶላር በላይ ስትከፍል ቆይታለች:: ገንዘቧን ከፍላም ቢሆን መጉላላቶች አሉባት:: የገቢዋም ሆነ የወጪዋ ሚስጥር የማይጠበቅ ነው:: እነዚህ ሁሉ ስብራቷ ሆነው ቆይተዋል::

> **የአፍሪካ ቀንድ ሲባል የሚታወቀው በግጭት ነው:: በቀጠናው ሀገራት ተሳስረው ተጣምረው፣ ዘላቂ ሰላምን፣ ዘላቂ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስምምነትን ማድረግ አልተለመደም**

ኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘቷ መፃኢ እድሏ በቀጠናው ላይ የሚወሰን መሆኑን ያሳየ ነው:: በቀጠናው ያለው ተለዋዋጭ የፖለቲካ የሀይል አሰላለፎችና ልዩ ልዩ ኩነቶች የሚከሰትበት በመሆኑ ብሄራዊ ፍላጎቷንና ጥቅሟ ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ ጉዳዮችን በቅርበት መከታተል እንድትችል ያደርጋታል:: ለወጪ ገቢ ንግዷ የተሳካ እድል ይፈጥራል:: ከምንም በላይ በአካባቢው ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም የነበራትን ተፅዕኖ ፈጣሪ ሚና መልሶ የሚያቀናጃት ይሆናል::

የጋራ ተጠቃሚነት ማዕቀፍ ውስጥ ያለፈው የኢትዮጵያ የባህር በር ተጠቃሚነት ጥያቄ ጉዞ ብዙ ነገሮች ተብለውበታል:: በተለይ የብዙ ህዝብ መኖሪያ ሆና ድንበሯ ከባህር ርቆ መቆለፉ ተጠቃሚነቷ ላይ ጫና ሲያሳድር ቆይቷል:: የባህር በር ተጠቃሚነት ጥያቄዋ ከህዝብ እና ከቆዳ ስፋት አንፃር ተገቢ ሆኖ የቆየ ነው:: አሁን ምላሽ ማግኘት መጀመሩ ከፖለቲካዊ እስከ ማህበራዊ ጉዞዋ በዛው ልክ የሚወስን ይሆናል::

በቀጠናው ያሉ ሀገራት የውስጥ የፖለቲካ ትኩሳቶች በሚፈጥሯቸው ኩነቶች አካባቢውን ወደ አለመረጋጋት እየወሰደ ባለበት በአሁኑ ሰአት፣ በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በሌላው አለምም መሰል ግጭቶች በስፋት እየታዩ ባለበት ወቅት ከሱማሌ ላንድ መንግስት ጋር የተደረሰበት የመግባቢያ ስምምነት ለአካባቢው ዘላቂ ሰላምም የሚኖረው ፋይዳ ትልቅ ነው ።

ይሄ ስምምነት ለሁለቱም ሀገራት፣ ለአካባቢው፣ ለአፍሪካና ለአለም ሁሉ የሚሰጠው ትርጉም ታላቅ ነው:: ሰላምን ከማስፈን ኢኮኖሚን ከማሳለጥ የህዝብ ለህዝብ ትብብርን ከማጎልበት አንፃር የሚታይ ለውጥን ያመጣል:: በተለይ ኢትዮጵያ ወታደራዊ ካምፕን መመስረት መቻሏ ጠንካራው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በቀጠናው የሚካሄዱ የሽብርና የባህር ላይ ውንብድና ድርጊትን እንዲከላከል ያስችለዋል:: ይህም ለአለም ሁሉ እረፍት ነው:: ለኢኮኖሚያዊ ውህደት መነሻ ሆኖ ቀስበቀስ አፍሪካ ለያዘችው ለ2063 አጀንዳ መሳካት ግንባር ቀደም ሚና ይኖረዋል::

ኢትዮጵያ በምትገኝበት የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ነገሮች በሚፈለገው መልኩ ሲሆኑ አልተመለከትንም:: በቀሪው አለም አካባቢው የሚታወሰው ባለመረጋጋትና ሰላም ማጣት ውስጥ መሆኑ የአደባባይ ሚስጢር ነው:: እናም አሁን ኢትዮጵያ በዚህ ደረጃ የምታደርገው ቀጠናዊ ተፅዕኖ ፈጣሪነት የባህር በር ስምምነት ድርሻ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም::

በጋራ መግባባት ውስጥ ተጠቃሚነት ትልቁን ድርሻ ይወስዳል:: በሀገራት መካካል የሚደረግ ስምምነት በዛው ልክ ቀጣይ የሚኖርን ቀጠናዊ አንድምታ መወሰኑ የሚካድ አይሆንም:: ሁለቱ አካላት ያደረጉት ስምምነት የሚገኙበትን አካባቢ ስምን መለወጥ ላይ አቅሙ ከፍ ያለ ይሆናል::

የአፍሪካ ቀንድ ሲባል የሚታወቀው በግጭት ነው:: በቀጠናው ሀገራት ተሳስረው ተጣምረው፣ ዘላቂ ሰላምን፣ ዘላቂ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስምምነትን ማድረግ አልተለመደም:: የቀጠናው ሀገራት እርስ በርስ በመተሳሰር ለኢኮኖሚ እድገት የበቁትን ሀገራት ተሞክሮ ሲወስዱ አይታይም::

ነገር ግን የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የብዙ የተፈጥሮ ሀብቶች ባለቤቶች ናቸው:: የአፍሪካም ሆነ የአለም ጂኦፖለቲክስ እየተቀየረ የሚሄደው በመሆኑ የሚያዋጣው አብሮ በጋራ መስራት መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል:: ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ ከሶማሌ ላንድ ጋር ያደረገችው የመግባቢያ ስምምነት እንደተሞክሮ የሚወሰድ ነው:: ከዚህ በኋላ በቀጠናው ትስስርን ማጠናከሪያ ማሳያ ነው::

40 በመቶ ቀጠናዊ የቆዳ ሽፋንና 80 በመቶ የህዝብ ብዛት ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ የምትወከልበት ቁጥራዊ ሀቅ ነው:: ከእሷ ጋር የሚደረጉ ስምምነቶች ትርፋቸው በዚህ አካባቢ ላሉ ሀገራትም ሲሆን ነው የቆየው::አሁን የተደረገው የወደብ ስምምነት ጥቅም በሂደት የሁሉም መሆኑ አይቀርም::

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሁሉንም የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የሚስብ አቅም ያለው ነው ። ይሄን የመሳብ በጎ አስተዋፅኦ /ፑል ፋክተሩን/ ማንም ሊያስቆመው አይችልም:: ስምምነት በወታደራዊ ፣ በመረጃና በመሰል ጉዳዮች ሌሎች የአካባቢው ሀገራትን በማገዝ ትብብር እንዲጠናከር ሊያደርግ እንደሚችልም ይታመናል ። ከህም ባለፈ ሀገራቱ ለጋራ እድገት በተለያ ዘርፎች አብረው የሚሰሩበትን አዲስ የትብብር ምእራፍ የሚከፍት ነው ።

በቀጣይም የአካባቢው ሀገራት ፤በመተማመንና በጋራ ተጠቃሚነት ከኢትዮጵያ ጋር ሊኖራቸው የሚችለው የትብበር ግንኙነት የቀጠናው ሀገራት ህዝብ ሁሉ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው ።ለዚህም ነው ኢትዮጵያ የሰጥቶ መቀበል መርህን በመከተል ሀገራት በራሳቸው ብቻ ሳይሆን አብሮ በሚደረግ ተሳትፎ ተጠቃሚነታቸንን እናረጋግጥ ስትል የቆየችው::

## አማራ ክልል

1ኛ ለ አቶ ተረፈ ፀጋዬ፣ 2ኛ ለወ/ሪት አመዘነች አየለ፣ 3ኛ ለአቶ አሰፋ ጎርፌ፣ 4ኛ ለአቶ ተስፉ አለሙ፣ 5ኛ ለአቶ ከበደ ጥላሁን ባሉበት በከሳሽ መተማመን አነስተኛ ብድር አቅራቢ ድርጅት እና በተከሳሽ በእናተ መካከል ስላለው የገንዘብ ክስ ክርክር ጉዳይ እርስዎ መሰስዎን አውቀው ለጥር 22 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ሰ/ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት 2ኛ ፍትሐብሔር ችሎት ቀርበው እንዲከራከሩ ፍ/ቤቱ አዟል። ሳይቀርቡ ቢቀሩ ግን ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ በመዝገቡ ላይ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ፍ/ቤቱ ያሳውቃል፡፡

**የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት /ደ/ብርሃን/**

በከሳሽ አቃቤ ህግና በተከሳሾች 1ኛ ሃቢብ እብሬ ሁሴን፣ 2ኛ መሐመድ አህመድ ይመር፣ 3ኛ ከድር አሸብር ዳምጠው በተከሰሱበት የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ክርክሩ ሊሰማ ለተቀጠረው ቀነ ቀጠሮ ለጥር 16/5/2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት ደሴ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት 1ኛ የወንጀል ችሎት እንዲቀርቡ የማይቀርቡ ከሆነ ግን ክርክሩን እንዳወቁት ተቆጥሮ በሌሉበት ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ፍ/ቤቱ አዟል።

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት የደሴ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት**

## ትግራይ ክልል

የባለንብረት ስም ገ/መድህን ገ/ማርያም የሠሌዳ ቁጥር ትግ 02-01-10461 የተሽከርካሪው አይነት ሞተር ብስክሌት የሻንሲ ቁጥር MD634K565K2G00123 ሞዴል APACHE-RTR የሞተር ቁጥር OE6GK2800149 የሊብሬ ቁጥር 1111 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ22/4/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ ይዞ እንዲቀርብ እያስታወቅን፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጣቸው መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመቐለ ከተማ ኮንስትራክሽን መንገድ እና ትራንስፖርት ቢሮ**

የባለንብረት ስም ክፍሎም በሪሁ ገ/ማርያም የሰሌዳ ቁጥር 02-5623 ትግ የሻንሲ ቁጥር MD625SF40H1A80112 ሞተር ቁጥር FF4AH1869355 የሊብሬ ቁጥር፣ 079326 ሞዴል TVS PHOENIX ከላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ ባለንብረት በ22/12/2015 ዓ/ም በኋላ የሰሌዳ ስለጠፋብኝ ምትክ ይሰጠኝ ብለው በማመልከቻ ጠይቀዋል። ስለዚህ ሰሌዳው ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትእዛዝ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ በአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን።

**በትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር የመቐለ ከተማ አስተዳደር መንገዝ ጽ/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም አመንሲስ አጀማ ተሰማ የሠሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B57962 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር JTDBW22E473123532 ሞዴል nze120l-AEMDKV የሞተር ቁጥር 2NZ-FE4205521 የሊብሬ ቁጥር 434970 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ27/4/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ ይዞ እንዲቀርብ እያስታወቅን፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጣቸው መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# Invitation to Bidders

## Tender RFQ ESLSE/COR/NEG/PRF/2022/00974

Ethiopian Shipping and Logistics would like to invite interested and eligible bidders for Semera Watch Tower, Office Renovation, Compound Work and Terminal Rehabilitation upon fulfilling of the following terms and conditions.

1. Bidders who engaged in the sector shall present renewed trade license, trade registration certificate, VAT registration, current tax clearance certificates, TIN certificate, Supplier list registration certificate and Renewed and relevant registration certificate on ministry of construction certification of competency for categories GC-5 or RC/BC-4 and above
2. Bidders shall register on our enterprise supplier list to access the tender document on our ERP System by using the link or register at Head Office in person 10th floor at procurement department upon fulfilling trade license certificate and TIN (Taxpayer Registration Certificate) starting from the date of this announcement in The Ethiopian Herald Newspaper.
3. The bid shall be valid for the period of 45 days after the system bid closing date in the system.
4. Bidder shall submit bid security in person at Head Office of the enterprise 10th floor procurement department and the amount of the bid security 500,000 (five hundred thousand) birr in the types of acceptable bid security. The type of acceptable bid security is unconditional bank guarantee or cash payment order (CPO). The bid security shall be valid for twenty-eight days (28) beyond the end of the validity period of the Bid Proposal Which shall be remained valid for a period of 45 days + 28=73.
5. To create better understanding on the bid document ESL will hold pre bid conference with all bidders on the 10th date of the floating of the bid by the newspaper or by next working day at ESL head office 10th floor procurement department.
6. The deadline for bid submission is date and time of ERP System.
7. Ethiopian Shipping & Logistics Services Enterprise reserves the right to accept or reject the bids partially or totally.

**For more information please call Tele 011-5-54-97-81/86**

**Web site: www.eslse.et**

**Ethiopian Shipping and Logistics Services**

# ማስታወቂያ

ኢትዮ ስኳር ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አ.ማ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ መንግሥት፣ ደቡብ ኦሞ ዞን፣ ሀመር ወረዳ በ10,000 (አስር ሺህ) ሄክታር መሬት ላይ ዘመናዊ ግብርና እየሠራ የሚገኝ እና የስኳር ፋብሪካ በመገንባት ላይ ያለ ኩባንያ ነው፡፡

ኢትዮ ስኳር ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አ.ማ 7ተኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ እና 7ተኛ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤውን የካቲት 16 ቀን 2016 ዓ.ም ቅዳሜ ዕለት ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ላይ በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ ያካሂዳል፡፡

ስለዚህም ሰርተፍኬት ያልወሰዳችሁ አዲስ አባላት በተጠቀሰው ቀን እና ሰዓት የገዛችሁበትን የባንክ ደረሰኝ ፣ ፎርም እና የታደሰ መታወቂያ እንዲሁም ሰርተፍኬት የወሰዳችሁ አባላት የታደሰ መታወቂያ ይዘው እንዲገኙ እናሳስባለን፡፡ በዕለቱ መገኘት የማትችሉ ህጋዊ ተቋም ጋር ቀርበው ውክልና በመስጠት በተወካያችሁ አማካኝነት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን።

ለተጨማሪ መረጃ በ0116160004/0116160003 በመደወል ወይም ቦሌ ጃፓን ማዞርያ ፊት ለፊት አፍሪካ ኢንሹራንስ ሕንፃ በሚገኘው ቢሮ በአካል መምጣት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**1. መደበኛ ጉባኤ አጀንዳ**

1.1 የጉባኤውን አጀንዳ ማፅደቅ

1.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርትን ማድመጥና በሪፖርቱ ላይ ተወያይቶ ሪፖርቱ ማፅደቅ

1.3 የኦዲት ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ

1.4 የስብሰባውን ቃለጉባኤ ማፅደቅ

**2. የድንገተኛ ጉባኤ አጀንዳ**

2.1 የአዳዲስ አባላትን ማመልከቻ መርምሮ ማፅደቅ

2.2 መተዳደርያ እና መመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻል

2.3 የስብሰባ ቃለጉባኤ ማፅደቅ

**ኢትዮ ስኳር ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አ.ማ**

# ባለውለታዎቻችን

# አቶ ተፈራ ሻውል ኪዳነቃል - ባለደማቅ አሻራ ዲፕሎማት

ክብረአብ በላቸው

ዲፕሎማሲ በሀገራትና መንግሥታት እንዲሁም በዓለም አቀፍ ተቋማት መካከል የሚካሄድ ዘርፈ ብዙ የውጭ ግንኙነቶች የሚከወኑበት ሁነኛ ጥበብ ነው። የዲፕሎማሲ ዋና ተግባር በአገራት መካከል ዓለም አቀፍ ግንኙነቶችን ማስተዳደር እና ሰላማዊ ግንኙነትን ማረጋገጥ ሲሆን የንግድ ስምምነት ድርድሮችን፣ በጋራ ችግሮች ዙሪያ ውይይትን፣ አዳዲስ ፖሊሲዎች መተግበርን እና አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታትን ያካትታል። ኢትዮጵያም የሺ ዓመታት ዲፕሎማሲ ልምድ እንዳላት ሀገር ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስከበር ስትጠቀምበት ቆይታለች።

ዲፕሎማሲ ወይንም የኹለትዮሽ ግንኙነት ማለት ሀገራት በሰላማዊ መንገድ እርስ በእርሳቸው ሀገራዊ ጉዳዮቻቸውን የሚፈጽሙበት እና ሰጥተው በመቀበል መርህ የየሀገራቸውን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስከብሩበት መንገድ እንደሆነ እሙን ነው።

በዚህ ፅሁፍ የሀገር ባለውለታ ብለን ታሪካቸውን የምናስነብባችሁ ሰው በአንድ በኩል በጋዜጠኝነት ያገለገሉ ሲሆን ረጅም ዘመናቸውን ደግሞ በዲፕሎማሲ የሰሩ ሰው ናቸው። ብስራተ ወንጌል ከዛሬ 59 አመት በፊት ሲጀመር ይህ ብስራተ ወንጌል ነው የሚለውን መክፈቻ ያሰሙ ናቸው። በጀርመን ፤ በካርቱም ፤ እንዲሁም በቼክ ሪፖብሊክ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው አገልግለዋል።

በተባበሩት መንግሥታት ለረጅም አመታት የሰሩ ናቸው። የቀድሞ ዲፕሎማት አምባሳደር ተፈራ ሻውል፤ ራሳቸው በአምባሳደርነት ከማገልገላቸው በላይ ልጃቸውም ወደዚህ ክቡር ሙያ እንዲሳብ በር የከፈቱ ሰው ናቸው።

በኢትዮጵያ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች ታሪክ ከማሟሻዎቹ አንዱ የሆነው የብስራተ ወንጌል ሬዲዮ ተመርቆ ስራውን ሲጀምር የተሰማው የመጀመሪያ ድምፅ የአምባሳደር ተፈራ ሻውል ነው። "ይህ የብስራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ ነው" ከግማሽ ከፍለ ዘመን በላይ ወደ ኋላ መለስ ብለው ወቅቱን ሲያስታውሱ 'ንጉሰ ነገስቱ ብስራተ ወንጌልን ሲመርቁ "ይህ የብስራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ ነው" ብዬ መጀመሪያ ቁልፉን ሲጫኑ ያበሰርኩት እኔ ነኝ' ይላሉ። በዚህ ቀደምትነታቸውም ኩራት እንደሚሰማቸው ይናገራሉ።

አምባሳደር ዲፕሎማትና የሚድያ ባለሙያ አቶ ተፈራ ሻውል ኪዳነቃል በጥቅምት 6 1936 ዓ.ም በሸዋ ዞን በሆለታ ነበር የተወለዱት። አለቃ ሻውል ኪዳነቃል ወላጅ አባታቸው ሲሆኑ እናታቸው ደግሞ ወይዘሮ ሳሳሁልሽ ኪዳኔ ይባላሉ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሆለታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በደብረብርሀን ተከታትለዋል። በመጨረሻም ወደ ደብረዘይት ተዘዋውረው ደብረዘይት ወንጌላዊት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ።

በሆለታ የንጉሱ የጦር ትምህርት ቤትን የተጎራበተ ልጅነታቸው ብዙ አሳይቷቸዋል… 'ጥይት ከመተኮስ በስተቀር ወታደሮቹ የሚያደርጉትን በሙሉ እናደርግ ነበር' ይላሉ ልጅነታቸውን እያሰቡ።

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በሆለታ አጠናቀው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በደብረ ብርሃን እንዳጋመሱ… እርሳቸው እንደሚሉት "በወቅቱ በነበረ ሽግሽግ…" በኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት እየተከፈለላቸው ደብረ ዘይት በሚገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ኮሌጅ በአዳሪነት እየተማሩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል። በደብረ ዘይት የነበራቸውን ቆይታ እንደሚወዱት ይናገራሉ። ለዚህም በሃገር ውስጥና በውጭ ሀገር መምህራን መማራቸው፣ ከመደበኛው የትምህርት ስርዓቱ ጎን ለጎን ተጨማሪ ክህሎቶችን መቅሰማቸው፣ በእረፍት ጊዜአቸው በይርጋዓለም ሆስፒታል የሚሰጡት የበጎ ፈቃድ ግልጋሎትና ሌሎችንም ቀበምክንያትነት ያነሳሉ።

የዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተማሪ በነበሩበት በአንድኛው ቀን፤ አዲስ ለሚቋቋም አንድ የሬዲዮ ጣቢያ ለድምፅ ፈተና የሚሄዱ ጓደኞቻቸውን ያገኟቸውና 'አብሬአችሁ ሄጄ ተፈትናችሁ እስክትወጡ ውጭ እጠብቃችኋለሁ' ብለው በአንድነት ወደ መፈተኛ ቦታው ያቀናሉ። ጓደኞቻቸውን የፈተነው ፈታኝ አይቷቸው ኖሮ አስገብቶ ፈተናቸውና ከተዘጋጁት ይልቅ ያልተዘጋጁት ተፈራ ሻውልን በአንደኝነት አሳልፎ በትርፍ ሰዓታቸው እንዲሰሩ ቀጠራቸው። አንዲት አንቀፅ ካነበቡ በኋላ የመጀመሪያ ክፍያቸው 25 ብር እንደነበረ ያስታውሳሉ።

ዜና አንባቢም ዜና ተርጓሚም ሆነው በብስራተ ወንጌል ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ ለከፍተኛ ትምርህት ወደ ጀርመን ሲያቀኑ፤ የሬዲዮ ጣቢያን በጋዜጠኝነት ስልጣን ባርኮ የመክፈት ታሪካቸው በዚያም ተደገመ። የጀርመን ድምፅ ዶቼበሌ የአማርኛው ክፍል ሲመሰረት አሻራቸው አለበት።

የጀርመን ቆይታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ የብስራተ ወንጌል ስራቸውን አጠናክረው ቀጠሉ። 'ለሃይማኖታዊ ስብከት ቢቋቋምም ሚዛናዊ ሚዲያ ነበር' ሲሉ በሚገልጡት እናት ቤታቸው በአማርኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ በድጋሜ ወደ ጀርመን የሚሄዱበት አጋጣሚ ተፈጠረ። ጀርመን ፍራንክፈርት ላይ በወንበዴዎች ቦንብ የተወረወረበት የኢትዮጵያ አውሮፕላን መጠነኛ እክል ገጥሞት ወደ ሃገሩ ከተመለሰ በኋላ የጀርመን ፕሬስ ስለኢትዮጵያ የሚፅፈው ጥሩ ያልሆነ ጽሑፍ ያሳሰባቸው የወቅቱ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አቶ ከተማ ይፍሩ፤ ችግሩን ለመፍታት በስልክ አስጠርተው 'እዚያው ስለተማርክ የግርማዊ ንጉሰ ነገስት ልዩ ጸሐፊ ሁነህ ቦን ከተማ ብትሄድ' እንዳሏቸው ያስታውሳሉ።

በወቅቱ ሀገር ውስጥ የነበራቸውን ኑሮ 'በጣም የተንደላቀቀ' ብለው የሚገልፁት ተፈራ ሻውል ይከፈላቸው ከነበረ ደመወዝ ከግማሽ በላይ ለሚቀንስ፣ ከጋዜጠኝነት ወደ አምባሳደርነት ለሚያሻግራቸውና ከእናት ሀገራቸው በአካልም ቢሆን ለሚያርቃቸው ሀገራዊ ተልእኮ 'ከሀገር በላይ ምንም የለምና' በማለት ይሁንታን ሰጡ። በጀርመን የተጣለባቸውን ተቀዳሚ ሀገራዊ ኃላፊነት ሲወጡ ቆይተው የ66ቱ ድርቅ ሲከሰት ለተጎጅዎች እርዳታ እንዲደረግ የበኩላቸውን እንደተወጡ ያስታውሳሉ።

በመቀጠልም ወደ ሱዳን ካርቱም ተዛውረው ሲሰሩ በሀገር ውስጥ የመንግስት ለውጥ ሁኖ የወቅቱ አለቃቸው ዳዊት አብዲ በደርግ ሲጠሩ አምባሳደር ተፈራ ጉዳይ ፈፃሚ ሆነው በዚያው ቆዩ። አስቀድሞ አለቃቸውን የጠራ ደርግ ድጋሜ እርሳቸውንም ጠርቶ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፕሬስ ጉዳይ ሃላፊ አድርጎ ሾማቸው፤ ቀጥሎ ደግሞ አሰራቸው።

3 ዓመታት ታስረው በተፈቱ በ3ኛው ቀን ኮሎኔል መንግስቱ ሀይለማርያም አስጠርተው በስህተት ስለመታሰራቸው ይቅርታ ጠይቀው "በምን እንካስህ" ብለው እንደጠየቋቸው ያስታውሳሉ። 'አንድ መሪ ስህተቱን አምኖ ለሀገሬ እንድሰራ እድል ከሰጠኝ ከዚህ በላይ ካሳ አልፈልግም' ብለው መመለሳቸውን አሁንም ድረስ አይረሱትም። የሰርቶ አደር ጋዜጣ አዘጋጅ እንዲሆኑ እድል ቢሰጣቸውም ባለመፈለጋቸው የቱሪዝም ኮሚሽን አማካሪ ሆኑ፤ ቀጥሎም የቀይ መስቀል ዋና ፀሐፊ ሆኑና በ77 ድርቅ ለተጎዱ ወገኖች ድጋፍ አሰባሰቡ።

በድርቁ ወቅት የነበራቸው አስተዋፅኦ ተቆጥሮ፣ ምስራቅ ጀርመን የነበሩት አምባሳደር የልብ ህክምና ሊያደርጉ መሆኑ ታስቦ ለ3ኛ ጊዜ ወደ ጀርመን ተላኩና መሉ አምባሳደር ሆኑ። በዚያ ለስሚንቶ፣ የጨርቃ ጨርቅና ሴራሚክ ፋብሪካዎች መቋቋምና ለበርካታ ተማሪዎች ስኮላርሽፕ መሳካት አብዝተው ጣሩ።ወደ ቸኮዝላቫኪያ ተዛውረው እየሰሩ እያለ ሌላኛው የመንግስት ለውጥ ሆነና ወደ ሀገር ቤት እንዲመጡ ተጠሩ።

በርካታ ወዳጆቻቸው እንዲቀሩ ቢመክሯቸውም ያለምንም ፍርሃት ጓዛቸውን ጠቅለው ወደ ሀገር ቤት ሲመለሱ የወቅቱ ባለስልጣናት 'ከዚህ የበለጠ አርበኝነት የለም' እንዳሏቸው ያስታውሳሉ። ለ3 ዓመታት በኢህአዴግ መንግሥት ስር ሰርተዋል።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአማካሪዎች መማክርት ጉባኤ አባል ሆነው የሚወዷት ሀገራቸውን ያገለገሉት አምባሳደር ተፈራ 3 ወንድ ልጆችን ስላፈሩበት ትዳር ሲጠየቁ 'ያኔ ደፋር ነበርኩ' ብለው ወደ ሚያስታውሱት የወጣትነት ዘመናቸው በትዝታ ይሄዳሉ።

በአቶ ከተማ ይፍሩ አማካኝነት ወደ ጀርመን ከማቅናታቸው ጥቂት ቀደም ብሎ ሽምግልና የላኩት የወቅቱ አለቃቸው የነበሩ ሻለቃ አሰፋ ለማን ጨምሮ ቢትወደድ አስፍሃ ወልደ ሚካኤል፣ ጀነራል ደረሴ ዱባለና ጀነራል ደበበ ኃይለ ሚካኤልን ነበር። የክብር ዘበኛ ምክትል የነበሩት ጀነራል ከበደ ዋጋዬ ሽምግልናውን ተቀብለው ያኔ አዲስ በነበረው ዋቢ ሸበሌ ሆቴል የተወሰኑ ሰዎችን ያሳተፈ ኮክቴል አድርገው ልጃቸው ወይዘሮ ወይንሸትን ለአምባሳደር ተፈራ ይሰጣሉ። ይህ በሆነ በማግስቱ 'አውሮፕላን ተሳፈርን' ይላሉ አምባሳደር ተፈራ ሻውል።

በሰርጋቸው ማግስት የተንደላቀቀ ያሉትን ኑሮ አስትቶ ባህር ያሻገራቸው፤ በስህተት 3 አመት አስሮ በፈታቸው መንግስት ስር ከ10 አመታት በላይ እንዲያገለግሉ ያደረጋቸው፤ ጡረታቸውን ሲቀሙ 'ይሁን ሀገሬን አልከስም' ያስባላቸው፤ የአማካሪዎች መማክርት ጉባኤ አባል እንዲሆኑ ሲጠየቁ በከፍተኛ ደስታና ኩራት እንዲቀበሉት ያስቻላቸው የፀና የሀገር ፍቅራቸው መሆኑን ይናገራሉ። 'እስር ቤቱ ይረሳል፤ የተደረገብህ ግፍ ይረሳል፤ ከሀገር የሚበልጥ ግን የለም' ይላሉ።

አቶ ተፈራ በ1950ዎቹ መጨረሻ ጋብቻ የመሰረቱ ሲሆን ሁለተኛው ልጃቸው አምባሳደር ሄኖክ ተፈራ በአሁኑ ሰአት የቦይንግ አፍሪካ ማኔጅንግ ዳይሬክተር ናቸው። ወደዚህ ሥራ ከመምጣታቸው በፊት በፈረንሳይ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ነበሩ። ዲፕሎማትነትን ከወላጅ አባቴ ከአቶ ተፈራ እያየሁ አደግኩ የሚሉት የዚህኛው ዘመን ዲፕሎማት ሄኖክ በፈረንሳይ ሀገር የህግ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ናቸው።

‹‹አባቴ ከሰው ጋር የመግባባት ልዩ ክህሎቱ ይደንቀኛል። ይህም ለአንድ ዲፕሎማት የግድ የሚያስፈልገው ነው። ሌላው አባቴ ሀገሩን ለማገልገል ያለው ፍቅር ለብዙዎች አርአያ የሚሆን ነው። ሁለገብ እውቀቱም ለብዙዎች የሚገርም ነው። ስለ ሀገሩ ብሎም ስለ አካባቢ ሁኔታ ጠንቅቆ አውቆ ነው የሚመራው ። በመሆኑም ብዙ ነገሮች ይሳኩለታል። በዚያ ላይ ከጋዜጠኝነት ወደ ዲፕሎማትነት የተሸጋገረ በመሆኑ የተግባቦት ክህሎቱ ልቆ የተገኘ ነው። በመሆኑም ዛሬ ላለሁበት ደረጃ አባቴ ያበረከተው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚነገር አይደለም። ›› ሲሉ ልጃቸው አምባሳደር ሄኖክ ስለ አቶ ተፈራ ማለትም ስለአባታቸው ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። አምባሳደር ተፈራ በአሁኑ ወቅት የ78 አመት ሰው ሲሆኑ በብዙዎች የሚከበሩ ላገራቸው ጥልቅ ፍቅር ያሳደሩ በወርቃማው ዘመን ሀገራችን ያፈራቻቸው ታላቅ ሰው ናቸው።

የቀድሞ ዲፕሎማት አቶ ተፈራ ሻውል ብዙ ያልተነገረለቸው ቢሆንም እርሳቸው ስራዬ ይናገር በማለት ብዙም ለመታየት የሚጓጉ አይደሉም። ነገር ግን በዘመናቸው የሰሩት ድንቅ ስራ ዛሬ በአዲሱ ትውልድ በበጎ ይወሳል። ዲፕሎማሲ በሀገራችን እንደ ዋና ህልውና በሚታይበት በአሁኑ ወቅት የእነ ዲፕሎማት ተፈራ ሻውል ግለ-ታሪክ ብዙ ትምህርት የሚቀሰምበት ነው። በተለይ ሚድያ እና ዲፕሎማሲን አንድ ላይ አጣምረው እውቀት ያከማቹ ታላቅ ሰው እንደመሆናቸው ኢትዮጵያ ብዙ ልትጠቀምባቸው የሚገቡ ሰው ናቸው።

የቀድሞ ዲፕሎማት አቶ ተፈራ ራሳቸውን ብቁ ዲፕሎማት ከማድረጋቸው ባሻገር ልጃቸውም የእርሳቸውን አርአያ ተከትሎ እንዲያድግ አድርገዋል። በዚህ ውጤታማ አባት ሊባሉ እንደሚገባም እሙን ነው። ኢትዮጵያ በወርቃማው ዘመን የኖሩ ብርቱዎቿን በወጉ መንከባከብ ፤ ታሪካቸውን በወጉ መዘከር አለባት። እንደ ዲፕሎማት አቶ ተፈራ ያሉ ሰዎች ተንቀሳቃሽ ቤተ መጽሀፍት እንደማለት ናቸው።

እኛም ለሀገራቸው በቅንነት እና በታማኝነት ያገለገሉ የሀገር ባለውለታዎች በሚዘከሩበት አምዳችን በዚህ ሳምንት የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ቀን ምክንያት በማድረግ በዘርፉ ሀገራቸውን ባለመታከት ያገለገሉትን አምባሰደር ተፈራ ሻውልን አመሰገንን፤ ረዥም ዕድሜና ጤናም ለእሳቸው ተመኘን።

**ኢትዮጵያ**
በወርቃማው ዘመን
የኖሩ ብርቱዎቿን
በወጉ መንከባከብ ፤
ታሪካቸውን በወጉ
መዘከር አለባት

